ተስፋ ለልጆች

የምስራቹ ቃል



ስም

_____

የመምህሩ መፅሐፍ

የፕሬዝዳንቱ ደብዳቤ

ልጆች ከፊታቸው ገና ያልተኖረ ረጅም ዘመን አላቸው፡፡ በሂዱበት ስፍራ ሁሉ ከሌሎች ሠዎች ጋር ይገናኛሉ፡፡ አንድ ልጅ (አንዲት ልጅ) በዕድሜ ዘመኑ/ኗ ከምን ያህል ሰዎች ጋር እንደሚገናኝ አስባችሁ ታውቃላችሁ) ዋናው ቁምነገር ልጁ (ልጅቷ) የወንጌልን እውነት ታጥቀው ከሆነ ይህ ወንጌል በሚሂዱበት ስፍራ ሁሉ ይከተላቸዋል፡፡

ልጆችን በሙላት በወንጌል መድረስ (‹ተስፋ ለልጆች› የምንለው ማለት ነው) ሕፃናትን በወንጌል ዕውቀት የማስታጠቅ ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ‹ተስፋ ለልጆች› የተሰኘው ስልጠና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ልጆችን ለክርስቶስ መማረክ ትልቅ አቅም ያለው ነው፡፡ ይህ ፕሮግራም ኢቫንጀሊዝም ኤክስፕሎሾን ኢንተርናሽናል እና ዋን ሆፕ ከተሰኙ ሁለት ሚኒስትሪዎች የተውጣጣ ሃሳብ ሲሆን እነዚህ ሚኒስትሪዎች በዓለም ዙሪያ ያሉ ልጆችን በወንጌል ለመድረስና ይህ እንዲሳካ ለማስተባበር ይሰራሉ፡፡

ልጆችን በክርስቶስ ወንጌል የመድረስ ጠቀሜታ ችላ ሊባል አይገባም፡፡ ልጆች የዛሬይቱና የወደፊቷ ቤተክርስቲያን ተረካቢ ኃይሎች ናቸው ልቅ ሊተዉ አይገባም፡፡ የሚያስፈልጋቸው የባህሪና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ብቻ አይደለም፡፡ ግላዊ ሕይወታቸው ላይ አምንታዊ ተጽዕኖ እስኪያመጣ ድረስ ወንጌልን ጠልቀው መረዳት እና ይህንንም ለሌሎች እንዴት እንደሚያካፍሉ ሊያውቁ ይገባል፡፡ ‘የኢቫንጀሊዝም ኤክሰንሎሾን’ ልጆች ለልጆች ያስተማሩትን ወንጌልን በመቀበል ለሌሎች ማካፈል እና እነዚያም የተካፈሉትን መልሰው ለሌሎች በማካፈል ለእግዚአብሔር መንግስት መስፋፋት በጐ ተጽዕኖን መፍጠር ነው፡፡

ልጆችን በወንጌል በማስታጠቅና በዓለም ዙሪያ ሁሉ ለሚገኙ በርካታ ሚሊዮን ሕፃናት ተስፋን በመስጠት ታላቅና አስቸጋሪ ሥራ ላይ በመሳተፍዎ እግዚአብሔር ይባርክዎት፡፡



ሬቨረንድ ጆን ቢ.ሶሬንሰን - የኢቫንጀሊዝም ኤክሰንሎሾን ኢንተርናሽናል ፕሬንዝዳንት

Hope for Kids Teacher's Book
EE-TB (Evangelism Explosion Teacher's Book): ISBN 978-1-59480-364-2
Copyright © 2010 Evangelism Explosion International

All rights reserved including translations. Not to be reproduced in any form, except where specifically noted, without prior written permission.

All Scripture quotations are taken from the HOLY BIBLE, NEW INTERNATIONAL VERSION®. NIV®. Copyright ©1973, 1978, 1984 by International Bible Society. Used by permission of Zondervan.
All rights reserved 3/2010

ዓለማቀፍ የወንጌል ትንታግ
ተስፋ ለልጆች የመምህሩ መጽሐፍ

ይዘት ገጽ

የኘሬዝዳንቱ ደብዳቤ ..... በውስጥ ሽፋን
ይዘት 1

ገለፃ 2

መግቢያ 2
ዓላማው 2
መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ተስፋ ለልጆች 2
ተስፋ ለልጆች የትምህርት አቀራረብ 3
የመማርና የማስታወስ ችሎታ ፒራሚድ 3
ተስፋ ለልጆችን ለማስተማሪያ ዘዴ 4
ተስፋ ለልጆች እንዴት ይሆናል? 4
የተስፋ ለልጆች ስልጠና መሠረታዊ ይዘቶች 5
ለተስፋ ለልጆች የቀረበ የትምህርት ዕቅድ 6

የማስተማሪያ ምዕራፎች 7

ምዕራፍ 1፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጨዋታዎች 7
ምዕራፍ 2፡ ቃለመጠይቅ 13
ምዕራፍ 3፡ የወንጌል መንገድ 17
ምዕራፍ 4፡ የምስራቹ ቃል 20
ምዕራፍ 5፡ እንነጋገር 24
ምዕራፍ 6፡ መንግስተ ሰማያት 31
ምዕራፍ 7፡ ኃጢአት 36
ምዕራፍ 8፡ እግዚአብሔር 40
ምዕራፍ 9፡ ክርስቶስ 44
ምዕራፍ 10፡ እምነት... 49
ምዕራፍ 11፡ መልስ 52
ምዕራፍ 12፡ በኢየሱስ ማደግ 55

ትግበራ 59

የተስፋ ለልጆች ትግበራ የመልመጃ መጽሐፍ 59
የልጆቹ የወንጌል ትንታግ ትምህርት የመንፈቅ ዓመት (የ6ወራት) ሰንጠረዥ 61

ተጨማሪ ማብራሪያዎች 62

የተስፋ ለልጆች የወንጌል መንገድ 62
የተሟላ ተስፋ ለልጆች የወንጌል መንገድ ሲተነተን 63
ዓለማቀፍ የወንጌል ትንታግ
የእምነት ዐንቀጽ እና መመሪያዎች 65
ዓለማቀፍ የወንጌል ትንታግ
ኢንተርናሽናል የእምነት መግለጫና መርሆዎች ....የጀርባ ሽፋን ውስጠኛ ገጽ

ገለፃ

መግቢያ

ልጆችን በወንጌል ለመድረስ ወደሚደረገው ተልዕኮ እንኳን ደህና መጡ፣ ይህ በዚህ ዘመን ከሚሰሩና እጅግ አስደሳች ከሆኑት አገልግሎቶች አንዱ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ይህ አገልግሎት የተዘጋጀው ኢቫንጀሊዝም ኤክስፕሎሸርን ኢንተርናሽናል በተባለ ድርጅት ነው፡፡ ኢቫንጀሊዝም ኤክስፕሎሸርን በወዳጅነት መንፈስ ሌሎችን በወንጌል ለመድረስ፣ በስነ-ምግባርና በጤናማ መንፈሳዊ ዕድገት ላይ የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡ ‹‹ተስፋ ለሕፃናት›› የሚለው አገልግሎት የሚጀምረው እኛ ለልጆች ወንጌልን በማስተማር ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደምንችልና እነርሱም በተራቸው የተረዱትን እውነት ለሌሎች ማካፈል እንደሚችሉ በማመን ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር መማር አስደሳችና አዝናኝ እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

ዓላማው ...

ዓላማው በዓለም ዙሪያ የሚገኙ በአዋቂነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች ለልጆች ወንጌልን ማስተማር እና መግለጥ እንዲችሉ ማስታጠቅ ነው፡፡

- ወንጌልን ለልጆች መግለጥ
- ልጆችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወደሚገኘው ደህንነት ማምጣት
- የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ መደገፍ ማለት ነው፡፡

የተስፋ ለልጆች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

- እያንዳንዱ ክርስቲያን ምስክር ሊሆን ይገባል፡፡ (ማር.1፡17, ሐዋ.1፡8)
- ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል ክርስቲያኖች የታጠቁ መሆን አለባቸው፡፡ (ኤፌ 4፡11-12)
- የተዋጣለት የማስታጠቅ ሥራ ሊሰራ የሚችለው በስራ ላይ ስልጠና ነው፡፡ (ማር.3፡14)
- በቀላሉ ነፍስን ከማሸነፍ ይልቅ ስልጡን የነፍስ አሸናፊዎች የበለጠ ጥቅም አላቸዉ።
  (2 ጢሞቲዮስ 2:2)
- ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፡፡ (መዝ.127፡3)
- ልጆች በጌታ ኢየሱስ ልብ ውስጥ የተለየ ስፍራ አላቸው፡፡ (ማርቆስ 10፡13-16)
- አዋቂዎች ስለ ወንጌል የተማሩትና የተረዱት እውነት ወደሚቀጥሉት ተከታታይ ትውልዶች መተላለፍ ይገባዋል፡፡ (መዝ 78፡1-7)
- ልጆች ወንጌልን በሚገባ ተገንዝበው ደህንነትን ገና ከልጅነት ዕድሜያቸው ሊለማመዱት ይገባል፡፡ (2ጢሞ. 3፡14-15)
- ልጆች ወንጌልን በመማር ለሌሎች ሊያካፍሉ ይችላሉ፣ ደግሞም ይገባቸዋል፡፡ (1ኛ ጴጥ. 3፡15)
- ለሕፃናት ጥሩ አርአያ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ገና በልጅነት እድሜው አባቱን ማገልገል ጀምሮ ነበር፡፡ (ሉቃ 2፡41-52)

እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች የሆኑ ፎር ኪድስ አገልግሎት ጽኑ መሠረቶች ናቸው፡፡ ይህን ለልጆች ማስተማሪያ መመሪያ መጽሐፍ ስታነቡም ሆነ ስትጠቀሙ እነዚህ መርሆዎች እንዴት እንደሚተገበሩ እንደምታዩ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

የተስፋ ለልጆች ትምህርት አቀራረብ

ትምህርቱን ስታቅዱ ልጆቻችሁ ከእናንተ ጋር በሚኖሩበት ወቅት ሊቀስሟቸው የሚገቡ የሕይወት ተሞክሮዎችን እያሰባችሁ መሆን ይገባዋል፡፡ ስለዚህ ይህንን ትምህርት የሚያስተምሩና የሚካፈሉ ሰዎች ሁሉ አመለካከትና ስሜት የትምህርቱን አሊያም የበለጠ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡

የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ዘይቤን የመማርና የማስታወስ ችሎታን የሚያሳይ ፒራሚድ

የሆነ ፎር ኪድስ የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ በማየት፣ በማዳመን፣ በእንቅስቃሴ፣ ነክቶ (ዳስሶ) በመለየት እና በህትመት ውጤቶች (መጽሐፍት) አማካኝነት ነው፡፡ ምንም እንኳን ልጆች ከአንዱ የማስተማሪያ ዘዴ ይበልጥ ሌላውን ሊወዱ እንደሚችሉ ቢታወቅም የተለያዩ የአቀራረብ ስነ ዘዴዎችን መጠቀም የትምህርት አሰጣጡን ሂደት ያፋጥናል፡፡ ስለዚህ ሆነ ፎር ኪድስ የተሟሉ በእይታ፣ በስዕላዊ መግለጫ፣ በውይይት እና የወንጌልን መንገድ ለልጆች ለማስተማር በሚካሄዱ ልምምዶች ይከናወናል፡፡ ለምሳሌ በእያንዳንዱ የትምህርት ምዕራፍ ከተማሩት ትምህርት መካከል በስዕላዊ መግለጫ የተደገፈውን አንዱን ትምህርት ወደ ቤታቸው ይዘው በመሄድ እንዲሰሩት (እንዲከልሱት) ሥራ ይሰጣቸዋል፡፡የተማሩትን ወደ ቤት ይዘው በመሄድ ለሌሎች እንዲያካፍሉም ይበረታታሉ፡፡ በውይይት፣ በክፍለ ትምህርቱ ወቅት በሚሰሩ ተግባራትና የቡድን ሥራዎች ሆነ ፎር ኪድስ ልጆች እርስ በርስ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ከማስቻሉም ባሻገር ከቡድን መሪዎቻቸውና ከመምህራንም ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል፡፡ወደ ቤት የሚወሰዱ ስራዎችንም በመስራት ከመጽሐፍት ጋር ይገናኛሉ፡፡ ታሪኩን መተረክ (ትረካ) አንዱ ተመራጭና የተዋጣለት የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ታሪኮች እና ስዕላዊ መግለጫዎች የወንጌልን መልዕክት ለልጆች ግልጽ ለማድረግ ይረዳሉ፡፡ ልጆቹ ስዕላዊ መግለጫዎችንና የወንጌልን መንገድ እየተለማመዱ ቃሉን በመካፈል መስተጋብር (ግንኙነት) ይፈጥራሉ፡፡

‹‹የመማርና የማስታወስ ችሎታ ፒራሚድ›› የተለያዩ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን በንጽጽር የሚያሳየን ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ልጆችን በማስተማር ሂደት ውሰጥ የምንከተለውን የተነቃቃ አቀራረብ ጠቀሜታ ያሣየናል፡፡

መማርና የማስታስ ችሎታ



1. ሆነ ፎር ኪድስ አብሮ መስራት ነው

በመጀመሪያው የትምህርቱ ክ/ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ኃይለኛና ጉልበታም መሆኑ ን ለልጆቹ እናስታውቃለን፡፡ ተያያዥነት ባላቸው ዝማሬዎችና ጨዋታዎች ላይ አብ ረው እንዲሳተፉ በማድረግ የወንጌል መንገድ አካል የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶ ች አዋዝተን እያቀረብን ልጆቹን በመማረክ በማዳመጥና በእንቅስቃሴ ታግዘው የመማ ር ችሎታቸውን በማዳበር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቃላቸው እንዲሸመድዱ መርዳ ት አለብን፡፡

ዊይይትና እንቅስቃሴዎች በትምህርት ሰዓትና የቡድን ሰዓት የእንክስቃሴ መዐዛፉን ሲጠቀሙ ህፃናቱ ከሌሎች ጋር እዲገናኙ እንዲሁም ከቡድን አስተማሪዎችና ከሌሎች አስተማሪዎች ጋር እንዲገናኙ ይረዳል። ሰርተዉ ወደቤት በሚወስዷቸዉ እቃዎች ግን ኙነት ይፍጥራሉ። ታሪክ ማዉራት ትምህርቱ ጠቃሚ እንዲሆን ይረዳል። ታሪኮችና ሥእላዊ መግለጫዎች ወንጌልን ለህፃናት ግልፅ ያደርጋል። ልጆችም በስእላዊ መግለጫ ዉ ወንጌልን ይጠቀማሉ ወንጌልንም ይማማራሉ።

2. ሆነ ፎር ኪድስ ዘላቂ ግንኙነት ነው

ሆነ ፎር ኪድስ ልጆች የቡድን መሪዎቻቸው ከሆኑት ወጣቶችና አዋቂዎች ጋር እንዲ ገናኙ እድል ይሰጣል፡፡ ልጆች ጠንካራ አርአያ የሚሆኗቸው ሠዎችን ይፈልጋሉ፡፡ እውነተኛ የሆኑና የሚታመኑ አዋቂ ሰዎችን በማግኘት ግንኙነት መፍጠር ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከወላጆቻቸው የሚታመኑባቸውና የሚደገፉባቸውን አዋቂ ሰዎች በማግኘ ት ቀና ግንኙነት መፍጠር ይፈልጋሉ፡፡ .

ሆነ ፎር ኪድስ እንዴት ተግባራዊ ይሆናል?

- የሆነ ፎር ኪድስ የአዋቂዎች ስልጠና ትምህርት መስጠት ለልጆች መሪዎች፣ ለመጋቢያን፣ መምህራንና ወላጆች

- የሰለጠነ የሆነ ፎር ድስ መሪ፣ ወይም የሆነ ፍር ኪድስ የልጆች አማካሪ ስልጠና ውን በአንድ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ ሆኖ ይመራል፡፡
- አዋቂዎችን የምናስታጥቀው፡
    1. ለልጆች ወንጌልን በግልጽ እንዲያብራሩ
    2. ልጆች ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን እንዲመጡ እና
    3. ልጆች ወንጌልን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ለማስታጠቅ እንዲችሉ ማብቃት ነው፡፡

<u>የሃገር ውስጥ (አካባቢያዊ) ስልጠናን</u>

ለልጆችና ለአዋቂ የቡድን መሪዎች መስጠት

- በየቤተክርስቲያኖቻችንና በየት/ቤቱ ላሉ ልጆች
- እናንተ (የሆነ ፎር ኪድስ መምህራን) በቡድን መሪዎቻችሁ እየታገዛችሁ ስልጠናውን ትመራላችሁ፡፡
- ልጆችን የምናስታጥቀው፡
    1. የወንጌልን መልዕክት እንዲገነዘቡ
    2. በክርስቶስ ኢየሱስ ወደሚገኘው የደህንነት እምነት እንዲመጡ
    3. ለሌሎች የወንጌልን እውነት እንዲያካፍሉ

የሆነ ፎር ኪድስ ስልጠና አበይት ትኩረቶች

ሆነ ፎር ኪድስ የተመሠረተው በዶ/ር ዲ.ጀምስ ኬኔዲ አማካይነት በተጀመረውና ኢቫንጀሊዝም ኤክስነሎሽን በተሰኘው ራዕይ ላይ በመመርኮዝ ሲሆን አቀራረቡም ሆነ ስነ ዘዴው ለየት ያለ ነው፡፡ ይህ ራዕይ የልጆችን ፍላጐት ለይተው በሚያስተምሩ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

1. የጸሎት አጋሮች

የጸሎት አጋሮች ወላጆች፣ ሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት፣ ወይም ክርስቲያን ወዳጆቻችሁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጸሎት አጋሮች ለአገልግሎቱ ኃይለኛ ድጋፍ ናቸው፡፡ ለልጆቹ እየጸለዩላቸው አብረው ይንበረከካሉ፡፡ ስለ ዕቅዶቻችሁ እና የቡድን መሪዎቻችሁም ይጸልያሉ፡፡

2. የቡድን መሪዎች

በሆነ ፎር ኪድስ ውሰጥ ያሉ ረዳቶች የቡድን መሪዎች ይባላሉ፡፡ እምነት የሚጣልባቸውና ኃላፊነት መሸከም የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ያለፈው ልምዳቸው (ስር መሠረታቸው) እና ለልጆች ያላቸው ፍቅር በመረጃ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ እነዚህ ሰዎች ወላጆች ወይም ሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አገልግሎቱን እና እያንዳንዱን ትምህርት ከመጀመራችሁ አስቀድሞ ኃላፊነትና የስራ ድርሻ ስጧቸው፡፡

3. ትምህርቶች

የሆነ ፎር ኪድስ ትምህርቶች አጫጭርና ተባብሮ በመስራት የታጀቡ ናቸው፡፡ መማር ተደጋጋሚና---------- ሂደት ነው፡፡ ወደ ቤት የሚወሰዱ ሥራዎችና ስዕላዊ መግለጫዎች ልጆቹ ከትምህርቱ የሚያገኙትን ግንዛቤ ይጨምርላቸዋል፡፡

4. የሆነ ፎር ኪድስ የወንጌል መንገድ

የሆነ ፎር ኪድስ ፋውንዴሽን ለልጆች ጐስነል ፓዝ ማስተማሪያ በተጨማሪነት የተያያዘ ነው፡፡

5. የስራ ላይ ስልጠና (ስላስ)

በሆነ ፎር ኪድስ ውስጥ የስራ ላይ ስልጠና (ስላስ) የሚጀምረው ልጆች በተሰጣቸው ድርሻ ላይ የተሳተፉበትንና የተማሩትን በማካፈል ነው፡፡ በዚህ መልኩ ልጆች ክርስቶስን በግል የማመን መረዳታቸውን እና ልምምዳቸውን ያዳብራሉ፡፡ የተማሩትን በቤትና በትምህርት ቤቶች እንዲያካፍሉ ይበረታታሉ፡፡ ይህም ወንጌልን የማካፈል ልምድ ይሰጣቸዋል፣ የቤት ስራ ክፍሎቹ ልጆች የተማሩትን ለማካፈል የመነሻ ነጥቦች ይሆኗቸዋል፡፡ የስራ ላይ ስልጠናው ግብ የህይወት መርህ ምስክርነት ነው፡፡ የልጆች እና ተስፋ ለሕፃናት የቡድን መሪዎች በስራ ላይ ስልጠና ጊዜ ትምህርት ቤቶችን፣ ሕፃናት ማሳደጊያዎችን፣ ፓርኮችን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ክበባትን ወይም የወንጌል ሥርጭት ሁኔታዎችን መጐብኘት ይችላሉ፡፡ በስራ ላይ ስልጠና የሆነ ቦታ በሚካሄድበት ወቅት ቦታው አስተማማኝ፣ የተስተካከለ እና ሙሉ ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

አስደሳቹ የስራ ላይ ስልጠና ሐሳብ ልጆች አስር የሚሆኑ ጓደኞቻቸውን በልዩ የእግዚአብሔር / ሰው በሚታዩበት ጊዜ በመጋበዝ ለማበረታታት ነው፡፡ ይህ የ15 ደቂቃ እርዝማኔ ያለው ‹አኒሜሽን› ፊልም የተዘጋጀው በአንድ ተስፋ ሲሆን የምስራቹን ቃል ለመንገር ወደር የማይገኝለት መንገድ ነው፡፡ ልጆች ፊልሙን ከተመለከቱ በኋላ ከጓደኞቻቸው ጋር ለመከፋፈል የተስፋ መንገድ የሚለውን መጽሐፍ ለእያንዳንዳቸው ይስጧቸው፡፡

.

ተመራጭ የሆነው የሆኘ ፎር ኪድስ የትምህርት ዕቅድ

የተስፋ ለሕፃናት የትምህርት ዕቅድ እያንዳንዱን ምዕራፍ ለማስተማር እንደ መምሪያ ያገለግላል

የትምህርቱ ግቦች

- እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የትምህርት ግቦች አሉት፡፡
- የማስተማሪያ ግቡ በማስተማር ወቅት ማሳካት የሚታሰበው ዋና አላማ ነው፡፡

እንኳን ደህና መጡ

- ልጆች እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡
- እያንዳንዱ ምዕራፍ የተለያየ መዋቅር እና የመግቢያ አስደናቂና ያልተጠበቀ ነገር ይ ይዛል፡፡

ፀሎት፣ ምስጋና እና ዝማሬ፡

- እግዚአብሔርን ማድነቅ፣ በእያንዳንዱ ትምህርት መጀመሪያ ላይ መፀለይ፣ ማመስገን እና መዘመር
- ፀሎት በተስፋ ለሕፃናት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለማስተማር ለመዘጋጀት ጊዜ እና በትምህርት ወቅት ለልጆች እና ከልጆች ጋር መፀለይ

ክለሳ

- ልጆችን ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን እንዲያካፍሉ እና በተጨማሪም የቤት ስራቸውን እንዴት እንደተጠቀሙበት እንዲያካፍሉ ማበረታታት፡፡
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንደገና ማስታወስ፡፡
- ሁልጊዜም ያለፈውን ክፍለ ጊዜ የትምህርት ነጥቦች መከለስ፡፡
- በተጨማሪ የወንጌል ጐዳንን መከለስ፡፡

የማስተማሪያ ነጥቦች

- የትምህርቱን ዋና ነጥቦች ማስተማር

ታሪኮች /ድራማ/ ማብራሪያዎች

- ልጆች በተሻለ የትምህርቱን ሐሳብ እንዲረዱት ለማድረግ ፈጠራ የተሞላባቸው ታሪኮችን መጠቀም እና እውነታውን በደንብ ማብራራት፡፡

መሸምደድ

- የወንጌል መንገድ የሽምደዳ ክፍሉን ከተግባር ጋር እንደገና ማስታወስ

የቡድን ሰዓት

- በቡድን ሰዓት ልጆች የተማሩትን እንዲያብላሉ ይረዳቸዋል፡፡ መረዳታቸውን ለማዳበር እና የመግለጽ ችሎታቸውን እንዲጨምሩ ያግዛቸዋል፡፡ በቡድን ሰዓት በተግባር መጽሐፉ ላይ ያሉትን ተግባራት ማጠናቀቅ እና የቤተ ሰራዊትን መስራት ለሽምደዳ እና ድርጊቶችን ለመለማመድ ይረዳል፡፡ በጋራ መጸለይ፡፡

የቤት ስራ (የተግባር መጽሐፉን አመሳክር)

- የቤት ስራው እንዴት የተማሩትን እውነት እንደሚያጠናክረው ማብራራት፡፡ የተማሩትን ለማስታወስና ለቤተሰብ እና ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ለማድረግ ነው፡ ፡ በእያንዳንዱ ትምህርት ላይ የቤት ስራ ስለ ኢየሱስ መናገራቸውን ምስክር መሆኑን በአጽንኦት ማስረዳት፡፡

ፀሎት እና ምስጋና

- ትምህርቱን በፀሎትና በመዝሙር መዝጋት

ምዕራፎቹን ማስተማር



ምዕራፍ 1፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጨዋታዎች

የትምህርት ግቦች

- ልጆች እና ወላጆቻቸው ወደ ተስፋ ለህፃናት እንዲመጡ ይበረታታሉ።።
- ልጆች በወንጌል መንገድ አማካኝነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ።።
- ልጆች የእግዚአብሔር ቃል ሃያል እና ሁልጊዜም እውነት መሆኑን ይረዳሉ።።

እንኳን ደህና መጡ፣ ፀሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

ልጆችን እና ወላጆቻቸውን ለመቀበል አካባቢውን ማስጌጥ

መምህራን እና የቡድን መሪዎች ዝግጅት ማድረግ

መግቢያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ጨዋታዎች ላይ የሚማሯቸው ጥቅሶች መሠረታዊ ናቸው።። እነዚህ ጥቅሶች የመንግስተ ሰማይ ኃጢአት፣ እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ እውነት እና ምላሽ የወንጌል መንገድ ደጋፊዎች ናቸው።። ጨዋታዎቹ፣ የተግባር ልምምዶቹ እና የቃል ጥቅሶቹ ቀልድን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የሚያዋዙ አዎንታዊ የማስተማር ዘዴዎች ናቸው።። የጨዋታዎቹ ዋና ዓላማ ልጆች በወንጌል መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ በሚማሩበት ወቅት እየተዝናኑ የሚያደርጓቸው ተግባራት ለመፍጠር ነው።።

የጨዋታ ዝግጅቶች

የተግባር ጨዋታዎቹን በክፍሉ አንደኛው ጥግ ላይ ማድረግ ይመከራል።። በሀ ቅርጽ መጠቀምም ሌላው አማራጭ ነው።። አካባቢውንም በደንብ ማስጌጥ ያስፈልጋል።። ከቤት ውጪ በቤተክርስቲያን ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ መጫወት ይቻላል።። የቡድን መሪውን የሰዓት ተቆጣጣሪ በማድረግ ፊሽካ ሲነፋ ከ3-5 ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲቀያየር ማድረግ።።

የመምህሩ ማስታወሻ

ልዩ ፍላጐት ያላቸው ልጆች ካሉ ማስተዋል ያስፈልጋል በተጨማሪም ጨዋታዎቹ እድሜን እና ባህልን ያገናዘቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ።።

የራስን ፈጠራ በማከል ጨዋታዎቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ወይም ለማብራራት ከተጠቀ ምንባቸው ሃሳባች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ።።

የትምህርቱ ነጥቦች

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡ ምሳሌ 3፡5-6

መምህሩ ምሳሌ 3፡5-6 ያለውን ጥቅስ በመሪነት ያስጠናል።። ከዚያም እግዚአብሔርን የምናደንቀው እና የምናመሰግነው በቃሉ መሆኑን ያብራራል።። ጥቅሱን በጋራ ከተግባር ጋር ማጥናት።። ይህን ጥቅስ በተስፋ ለሕፃናት ትምህርት ላይ እንደ መግቢያ አዘውትሮ መጠቀም።።

ምሳሌ 3:5-6

በሙሉ ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ። በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጐዳናህን ያቀናልሃል።

መግቢያ፡ የታሸገ ኃይል (የተግባር መጽሐፍ የስራ ገፆች)

ትምህርት ከመጀመርህ በፊት ከባትሪ ውስጥ ባትሪ ድንጋዮቹን አውጣቸው። ይህም ያለ ኃይል ማመንጫ ብርሃን ሊኖር እንደማይችል ማሳያ ይሆናል።

የተከበራችሁ እንግዶቻችን፣ ወንድሞች እና እህቶች እንኳን ደህና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጨዋታ በሰላም መጣችሁ። መልካም ጊዜ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።



ዛሬ በወንጌል መልዕክት ውስጥ ጠንካራ እውነትነት ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንማራለን። እነዚህ ጥቅሶች በ‹‹ሐይል ከረጢት›› ውስጥ ይገኛሉ። የሐይል ከረጢት የሚል ስያሜ የተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ሃያል ስለሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት፣ ለተግሳጽ፣ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል›› (2ጢሞ 3፡16)። ገና በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፍጥረትን በቃሉ ሐይል ፈጥሯል። የእግዚአብሔር ቃል ሕያል ነው ልብን፣ ህይወትን ይቀይራል። ልክ ባትሪ ድንጋይ ያለው ባትሪ ጨለማን አሸንፎ እንደሚያበራ (ባትሪውን አብርተህ ያዝ) ስለዚህ በሐይል ከረጢቱ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች እንማራለን ጥቅሶቹ የሰዎችን ህይወት በእግዚአብሔር እውነት የሚያበራ ሐይል ይሰጣሉ።

ከጨዋታ በፊት መመሪያ/ ደንብ

መምህሩ የእያንዳንዱን ጨዋታ ስርአቶች/ ደንቦች ያብራራል

- በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በትንንሽ ቡድኖች መከፋፈል። በየቡድናችሁ በማብራሪያው መሠረት ወይም የቡድን መሪው ባሳየው መሠረት መጫወት። በዚህ ጊዜ ጥቅሶችን ቢያንስ ሶስት ጊዜ በቃል ማለት። ፊሽካው በሚሰማበት ጊዜ ወደ ሚቀጥለው ጨዋታ ማለፍ።
- ቡድኑ የሚኖረው የተወሰነ ደቂቃ ስለሚሆን ሁሉም የቡድኑ አባላት በጨዋታው በፍጥነት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ማድረግ።
- ፊሽካው በሚሰማበት ጊዜ ወደሚቀጥለው ጨዋታ በማለፍ በመመሪያው መሠረት ወደ ጨዋታው መግባት። ከየት እንደምትጀምሩ አትጨነቁ። ሁሉም ቡድን እያንዳንዱ ጨዋታ ይደርሰዋል። (በእያንዳንዱ ጨዋታ ላይ የሚያግዝ መሪ ምረጡ)
- ትኬት ወይም የቃል ጥናት ጥቅስ- ጨዋታውን ከጨረሰ በኋላ እያንዳንዱ ልጅ ትኬት ወይም የቃል ጥናት ጥቅስ በሽልማት መልክ ይሰጠዋል።
- ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት በቡድን እንከፋፈላለን።
- ከአስር በላይ ቡድኖች ሊኖር አይችልም ወይም ስድስት ቡድኖች በአማራጭነት የቀረቡት ጨዋታዎች ከሌሉ ሊኖሩ ይችላሉ።

የተጠቆሙ ጨዋታዎች

- **ጨዋታ 1፡ መንግስተ ሰማይ**
  ‹‹የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ህይወት ነው..›› (ሮሜ 6፡23)

  <u>ኳስ ማንጠር ወይም መጣል</u>
  መሪው ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ጥቅሶቹን ለቡድኑ አባላት ያስታውሳል፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ኳሱን ወደ ላይና ታች ያነጥራል፡፡ ወደ ሚቀጥለው ልጅ ከማለፉ በፊት ተረኛው ልጅ ጥቅሱን ሶስት ጊዜ ይለዋል፡፡ ቀለበት የመሰለ ነገር ማዞርም አማራጭ ነው፡፡

- **ጨዋታ 2 መንግስተ ሰማይ (በምርጫ)**
  ‹‹ፀጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም››፡፡ (ኤፌ 2፡8-9)

  <u>የኮርማ አይን/ የአሳማ ልምምድ</u>
  ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ኤፌ 2፡8-9 እንደገና ያንብብ፡፡ ጥቅሱ በሚባልበት ጊዜ እያንዳንዱ ልጅ ሶስት ኳሶችን ወደ አሳማው ይወረውራል፡፡ በአማራጭነት ክብ ምልክት መሬት ላይ በመስራት ሳንቲም ወይም እምነበረድ መጫወት ይቻላል፡፡

- **ጨዋታ 3፡ ኃጢአት**
  ‹‹ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል›› (ሮሜ 3፡23)

  <u>ሰኞ ማክሰኞ ጨዋታ</u>
  ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሶቹን እንደገና ያነባል፡፡ የመጫወቻ መስመሮቹን በመሬት ወይም በግድግዳ ላይ በመሳል ጥቅሶቹን በቦታዎች ላይ መጻፍ፡፡

  እያንዳንዱ ልጅ ጥቅሱን በማለት በየራሳቸው ዙሮች ጨዋታውን ይጫወታሉ፡፡



ጨዋታ 4፡ ኃጢአት (በምርጫ)

እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ (ማቴዎስ 5፡48)

<u>ርዝመት ዝላይ</u>

ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሶቹን እንደገና ያነባል፡፡ እስከ አምስት ሜትር (አስራ አምስት ጫማ) ርዝማሬ ያለው መዝለያ ይዘጋጃል፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ከመጀመሪያው መስመር ወደ አስራ አምስት ጫማ (አምስት ሜትር) ርቀት ወዳለው ሁለተኛው መስመር ይዘላል፡፡ የቡድን መሪው እያንዳንዱን ዝላይ ይመዘግባል፡ ፡ የዝላዩ ርዝመት በማንኛውም ልጅ በትክክል ሊዘል አለመቻሉን ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን የቦታ እጥረት ካጋጠመ ወደ ጎን በማዘለል ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣው ተጫዋቹን ማወቅ ይቻላል፡፡

- ## ጨዋታ 5፡ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፡8)

የሶስት እግር እሽቅድድም

ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሱን እንደገና ያነባል፡፡ እያንዳንዳቸው ተጫዋች ልጅ እንዲጣመሩ ከተደረገ በኋላ የውስጥ እግራቸው ከሶስት እግር እሽቅድድም ጋር ይታሰራል፡፡ ልጆቹ የተወሰነውን ርቀት በሚጓዙበት ወቅት ‹‹እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ ነገር ግን ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ እንዲሁ አያልፍም›› የሚለውን ጥቅስ እያነበቡ እና እያጠኑ ይሄዳሉ፡፡

- ## ጨዋታ 6፡ እግዚአብሔር (በምርጫ)

‹‹አይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም፡፡››

ውስብስብ መንገድ ጨዋታ

የውስብስብ መንገድ ጨዋታን ለመጫወት በወለሉ ወይም በመሬት ላይ በጠመኔ ወይ ም በሌላ በሚጽፍ ነገር ውስብስብ መንገድ ይሰራል፡፡ በመቀጠል የቡድኑ አባላት ጥቅሱን ሲሉ ተረኛው ልጅ ከጥቅሱ እኩል በተሳለው ውስብስብ መንገድ ይራመዳል፡፡ የቡድን አባላቱ ጥቅሱን እስኪጨርሱ ድረስ መሻት ወይም መውጣት አይቻልም፡፡

- ## ጨዋታ 7፡ ክርስቶስ

‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔ ር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ሁሉ እንዲህ ወዶታልና፡፡›› (ዮሐ 3፡16)

ገመድ ዝላይ

ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሱን ይደግማል፡፡ ልጆች ገመድ እየዘ ለሉ እዛው ጥቅሱን አብረው ይላሉ፡፡ በገመዱም ፋንታ እንጨት ነገር መጠቀም ይቻላ ል፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ጥቅሱን በቃሉ እያለ ገመዱን ወይም እንጨቱን ይዘላል፡፡ ሁሉም ልጅ ከአንዱ እንጨት ወደ ሌላው እየዘለለ እስኪጨርስ ድረስ ጥቅሱን በማለት ይጫወታል፡፡

- **ጨዋታ 8 ክርስቶስ (በምርጫ)**

  ‹‹እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ›› (ኢሳይያስ 53፡6)

  ሚዛን መጠበቅ

  ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሱን ካነበበ በኋላ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ከኢየሱስ ላይ እንደጣለ ያብራራል፡፡ ትንሽ ከረጢት ነገር በእያንዳንዱ ልጅ ጭንቅላት ላይ ይቀመጣል፡፡ እያንዳንዱ ተጫዋች የተሸከመውን ከረጢት ሳይጥል ሚዛኑን በመጠበቅ እስከመጨረሻው መስመር ይጓዛል፡፡ ሚዛኑን ስቶ የወደቀበት ልጅ ከእንደገና መጀመር ይኖርበታል፡፡ በከረጢቱ ፋንታም ውስጡ የተጠቀጠቀ አሻንጉሊት እንደ አማራጭ መጠቀም ይቻላል፡፡

- **ጨዋታ 9፡ እምነት**

  ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ አመን አንተ እና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ፡፡›› (የሐዋ.16፡31)

  የእግር ዱካ

  ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የቡድን መሪው ጥቅሱን ያነባል፡፡ በመቀጠል ሶስት የእግር ምልክት (ዱካ) በእርምጃ መልክ ያስቀምጣል (ይስላል)፡፡



እያንዳንዱ ልጅ በእግር ዱካው በመተካት (በቡድኑ) የቃል ጥናቱን ጥቅስ ይደግማል፡፡

- **ጨዋታ 10፡ ምላሽ**

  ‹‹በእኔ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው፡፡›› (ዮሐ 6፡47)

  ለኢየሱስ መዝለል

  ጨዋታውን ቡድኖቹ ከመጀመራቸው በፊት የቡድን መሪው ጥቅሱን ያነባል፡፡ ልጆቹ መጀመሪያ ወደ ተሳሉት የእግር ምልክትና ጥቅሱን በቃላቸው እያሉ ምልክቶቹን ይይዛሉ (ይወጣሉ)፡፡

የቤት ስራ

- **የሐይል ከረጢት (የተግባር ስራ ገፆች)**
  ለቤተሰቦቻቸው እና ለጓደኞቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያካፍሉ የሐይል ከረጢት ክፍሉ እንደ ማስታወሻ ያገለግላቸዋል፡፡ ልጆቹን እንዲለማመዱ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን እንዲያካፍሉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ፡ የአንተን ቃል በመማር ስላሳለፍነው ድንቅ ጊዜ እናመሰግንሃለን፡፡ አንተን እና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን ቃልህን እንድንወደው እርዳን፡፡ አሜን!



መንግስተ ሰማይ
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ህይወት ነው...፡፡ ሮሜ 6፡23



ኃጢአት
ሁሉም
ኃጢአት ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐሏቸዋል፡
፡ ሮሜ 3፡23



እግዚአብሔር
እግዚአብሔር
ፍቅር ነው፡፡
1ዮሐ 4፡8
ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ
አይተውም፡፡ ዘሁ 34፡7



ክርስቶስ
በእርሱ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም
ህይወት እንዲኖረው እንጂ
እንዳይጠፋ እግዚአብሔር
አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ
ዓለምን እንዲሁ ወዷልና፡፡
ዮሐ 3፡16



እምነት
በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
እመን አንተና ቤተሰቦችህ
ትድናላችሁ፡፡ የሐዋ.16፡31



ምላሽ
በእኔ የሚያምን የዘላለም ህይ
ወት አለው፡፡ ዮሐ 6፡47



‹‹እኔ ነኝ››

በተግባር መጽሐፍ የውስጠኛው ሽፋን ገጽ

የትምህርት ግቦች

- መምህሩ የልጆቹን መንፈሳዊ ሁኔታ እና መረዳት ይመረምራል፡፡
- በልጆች እና መሪዎች መካከል ትስስር መፈጠር አለበት፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔር ቃል / መጽሐፍ ቅዱስ ሃይለኛ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን መረዳት አለባቸው፡፡

እንኳን ደህና መጡ፣ ጸሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

የቡድን መሪዎቹ ትልልቅ መነጽር እና ትልልቅ ጆሮዎች በማጥለቅ ለልጆች ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡

ክለሳ

ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ጥቅሶች በመከለስ እና ልጆቹን በመጠየቅ እንዴት የቤት ሥራ ቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት መጠየቅ፡፡

ሮሜ 6፡23 እንደመግቢያ መዝሙር በመጠቀም ማስተማር፡፡ መምህሩ ሮሜ 6፡ 23 እንደገና ካነበበ በኋላ በመዘመር ልጆቹ በአንድ ድምጽ መዝሙሩን እንደገና በህብረት እንዲዘምሩ ማድረግ፡፡

ትኩረታችሁ ወደዚህ ይሁን! (መሪው ብቻ) ግራ፣ ቀኝ፣ ግራ፣ ቀኝ፣ ግራ፣ቀኝ (በህብረት)
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው (መሪው ይለዋል፣ ቡድኑ ይደግማል)
የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ የዘላለም ህይወት ነው (መሪው፣ ቡድኑ) ሮሜ 6 እና 23 መሪ፣ የቡድን አባላት አሁን ምን እንደሆነ ንገሩኝ (መሪ፣ ቡድን አባላት) ህይወት፣
ሞት፣ ህይወት፣ ሞት፣ ህይወት (በህብረት)

የማስተማሪያ ነጥቦች

መግቢያ፡ እግዚአብሔር እና ቃሉ

እግዚአብሔር ሊሰማን ይወዳል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ማውራት የምንችለው ደግሞ በጸሎት ነው፡፡ እግ ዚአብሔ ደግሞ የሚያዋራን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሚናገረው ቃሉ ላይ ነው፡፡ ቃሉን በማንበብ ከእግዚ አብሔር ልንሰማ እና እግዚአብሔርን የበለጠ ልናውቀው እንችላለን፡፡ በቃሉ ውስጥ ማን እንደሆነ እናያ ለን (የልብ ቅርስ ያለው ምስል ማሳየት)፡፡ እግዚአብሔርን በምንሰማበት ጊዜ አይናችንን ጆሮአችንን ከልባችን ጋር አንስተን እንሰማዋለን፡፡ ቃልንህ በልቤ ሰወርሁ (መዝ 119፡11)

በተስፋ ለህፃናት ልጆችን በደንብ ማወቅ እንፈልጋን ስለዚህም ጥቂት ጥያቄዎችን በደንብ እንድንተዋወ ቅ እንጠይቃችኋለን፡፡

ማብራሪያ፡ ማድመጥ እና ማየት

መምህሩ ትልቁን መነጽር እና ትልቁን ጆሮ ለጥቂት ጊዜ በማድረግ የመስማትና የመመልከት ን ጽንሰ ሃሳብ ለማብራራት ይሞክራል፡፡ የቡድን መሪዎቹ የበለጠ መማር እንዳለባቸው አጽን ኦት ሰጥቶ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የቡድን መሪዎች ልጆቹን ጥያቄ በመጠየቅ መልሳቸውን በጥንቃቄ ያደምጣሉ፡፡

ቃለ ምልልስ፡ ‹‹እኔ ነኝ››

የቡድን መሪዎች የቡድን አባላቶቻቸውን ለመጠየቅ ወደየቡድናቸው ይመለሳሉ፡፡ ከቡድን አባ ሎቻቸው ጋር በጓደኝነት መንፈስ በመቀራረብ ለጥያቄዎቹ አመቺ በሆነ ግንኙት መጀመር አለ ባቸው፡፡ አንደኛው የቡድን አባል በሚጠየቅበት ወቅት ሌሎቹ የቡድን አባላት ትልልቅ መነጽ ሮችና ጆሮዎችን ይሰራሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ‹‹ይህ እኔ ነኝ›› የሚለው ን የመጠየቂያ ወቀት መጠቀም ይቻላል፡፡ በተግባር መጽሐፋቸው ሽፋን የውስጠኛው ገጽ ላይ የራሳቸውን ስዕል ልጆች እንዲስሉ አድርጓቸው፡፡

(ማስታወሻ፡ ከትምህርት ክፍለ ጊዜው በኋላ መምህሩ የልጆቹን መልሶች ከቡድን መሪዎቹ ጋር በመሆን ይከልሳል፡፡ እንዴት ባለ ጊዜ እና ሁኔታ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት እንደሚቻል ከ ቡድን መሪዎቹ ጋር ይወያያል፡፡ የተስፋ ለህፃናት የመጠየቂያ ወረቀትን በሚቀጥለው ትምህር ት 11 ለማመሳከሪያነት ሊያስፈልግ ስለሚችል መያዝ ያስፈልጋል)

የቡድን ሰዓት

- ‹‹እኔ ነኝ›› የሚለው የተግባር መጽሐፍ ላይ ያለውን ተግባር መፈጸም
- በጋራ መጸለይ

የቤት ስራ

ማስታወሻ፡ እያንዳንዱ የቤት ስራ የተማሩትን ለማብራራት ያስፈልጋል፡፡

- ትልልቅ መነጽሮችና ጆሮዎች (የተግባር መጽሐፍ የቤት ስራ ገፆች)

በመጀመሪያ የልጆቹን የመጀመሪያ የቀለም ምርጫ በመመልከት መነጽሮቹን እና ጆሮዎቹን በመቁረጥ ማጣበቅ፡፡ በመነጽር እና በጆሮቻቹ ጀርባ ላይ ልጆች ስማቸውን እንዲጽፉ ማድረግ፡ ፡ እነዚህ ትልልቅ መነጽሮች እና ጆሮዎች የቤት ስራ ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔርን እና ሌሎችንም በጥንቃቄ መስማትና ማየት እንዳለብን ያሳስበናል፡፡ ሁለት ጆሮዎችና አንድ አፍ የኖረን ለምን ይመስላችኋል) የምናወራውን ሁለት እጥፍ እንድንሰማ ነው፡፡

ልጆቹ ከመበተናቸው በፊት ስለ መነጽሮቹ እና ጆሮዎቹ ምንነት ለሌሎች እንዲያካፍሉ እና ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ቃል በደንብ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ፡ ስለምትወደን እናመሰግንሃለን፡፡ እኛ ማን እንደሆንን በትክክል ታውቃለህ፡፡ በደንብ እንድናውቅህ እና እንድንወድህ እርዳን፡፡ በኢየሱስ ስም ፀለይን፡ ፡ አሜን!

ይህ እኔ ነኝ

ስም
እድሜ

1. ስለ እግዚአብሔር ምን ልትናገር ትችላለህ?

2. ኃጢአት ምን ይመስልሃል?

3. ኢየሱስ ማነው?

4. ስለ መንግስተ ሰማያት ምን ልትነግረኝ ትችላለህ?

5. አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ምትሆን በእርግጥ ታውቃለህ?

6. እግዚአብሔር ለምን ወደ መንግስተ ሰማይ እንድትገባ አደርጋለሁ ቢልህ ምን ብለህ ትመልሳለህ?



ምዕራፍ 3፡ የወንጌል መንገድ



የትምህርት ግቦች

- ልጆች ትክክለኛውን የወንጌል መንገድ ይማራሉ
- ልጆች ስድስቱን ዋና ዋና የወንጌል መንገዶችን በእንቅስቃሴ መናገር ይችላሉ።

እንኳን ደህና መጡ፣ ፀሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

አዲስ ጓደኛ (አሻንጉሊት) በክፍሉ ፊት ላይ ይቀመጣል

ክለሳ

ያለፈውን ትምህርት በመከለስ ልጆቹ የቤት (መነጽር እና ጆሮዎች) ስራቸውን እንዴት የተማሩትን ለሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት ይጠይቃል፡፡

የማስተማሪያ ነጥቦች

ማስተዋወቅ፡ አዲስ ጓደኛ (ሰው ወይም አሻንጉሊት ሊሆን ይችላል)

በዚህ ክፍል ጊዜ አዲስ ጓደኛ አስተዋውቅ፣ ልጆች በደንብ እንዲያውቁት ስምም ይሰጠው፡፡ ይህ አዲስ ጓደኛ (ሰው ወይም አሻንጉሊት ሊሆን ይችላል) የበኩሉን አስተዋጽኦ ይጫወታል፡፡ አዲሱ እንግዳ ወንጌል መስማት እንደሚልግ ይሽውም የምስራች ቃል ሲሆን እግዚአብሔር ኢየሱስ በማመን ብቻ የዘላለም ህይወት እን ድናገኝ መፈለጉን እና መፍቀዱን ነው፡፡

ማስተዋወቅ፡ ወንጌል ማለት የምስራች ቃል ማለት ነው

ወንጌል ማለት የምስራች ቃል ነው፡፡ የምስራች ቃሉ እግዚአብሔር ኢየሱስን በማመን ብቻ የዘላለም ህይወት በመስጠት ሊያድነን መፈለጉ ነው፡፡ ይህ ማንም ሊሰማው የሚባ መልካም ዜና ነው፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንት ስለዚህ መልካም ዜና (የምስራች ቃል) በደንብ እንማራለን፡፡

ዛሬ የስድስተኛውን የወንጌል መንገድ ደረጃ እንማራለን፡፡ ይህ የትምህርታችን የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን አሁን መጀመራችንን ከጉዳዩ ጋር በቅርብ ለመታየት ይረዳናል፡፡ የወንጌልን ጭዳና ከተማርን በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በታሪኮች እንጠናክረዋለን፡፡ በተጨማሪም እንዴት ወንጌል እንደምንመሰክር/ እንደምናካፍል እንማራለን፡፡

መሸምደድ፡ የወንጌል መንገድ

የወንጌል ጐዳናን በመሰረታዊ የእጅ እንቅስቃሴ በማስተማር ልጆች ደጋግመው እንዲ ለማመዱት ማድረግ፡፡



ድራማ፡ የወንጌል መንገድ

(ጥቆማ፡ መምህሩ የወንጌል መንገድን በሚያስተምር ወቅት ሁለት ሰዎች አቋርጠው በመግባት ይቀልዳሉ ይህ ያልተጠበቀ ነገር ለመጨመር አስፈላጊ ነው፡፡)

1ኛ ሰው፡ እንደጠፋበት ሰው፣ ፀጉሩን በማከክ፣ ትከሻውን በመስበቅ

2ኛ ሰው፡ የጠፋብህን ትመስላለህ ልርዳህ)

1ኛ ሰው፡ እባክህ ወደ ሱዛን ቤት ለመሄድ ፈልጌ ነበር ግን አቅጣጫው ጠፋብኝ

2ኛ ሰው፡ ሱዛን ጓደኛዬ ናት፤ እንደምትኖር አውቃለሁ፡፡ ከዚህ ብዙ አይርቅም ይሄ መንገድ ይታይሃል)

1ኛ ሰው፡ ኦ! በጣም ጥሩ፣ ወደዚያ ነው የምሄደው)

2ኛ ሰው፡ አዎን፡፡ ይህን መንገድ ተከትለህ ሂድ ከዛ አቀበቱን ውጣ፡፡ ጫፍ ላይ ስትደርስ የሱዛንን ቤት ታየዋለህ፡፡

1ኛ ሰው፡ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ይህን አቅጣጫ ተከትዬ ብሄድ የሱዛንን ቤት ለማግኘት ይቀለኛል፡፡

2ኛ ሰው፡ ደህና ሁን፡፡

አቅጣጫን ማወቅ ወዴት እንደምንሄድ ለማወቅ ይረዳናል፡፡ የወንጌል መንገድም ልክ እንደዚ ሁ አቅጣጫ አመላካች ነው፡፡ ወንጌልን በመማርና ለሌሎች በማካፈል ወደ ትክክለኛው ጐዳና ይመራናል፡፡ የወንጌል ጐዳና ለምንሄድበት አቅጣጫ ግልጽና ቀላል የሆነ መንገድ ይፈጥርልና ል፡፡ ወደ መድረሳችን እንድንደርስ ይረዳናል፡፡

ማብራሪያ፡ የወንጌል መንግድ

የወንጌል መንግድ ማስታወቂያ ወረቀት መስራትና መለጠፍ፡፡ ይህ ማስታወቂያ መንግስተ ሰማይ፣ ኃጢአት፣ እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ እምነት፣ ምላሽ የሚሉ ፅሁፎች ይኖሩታል፡፡ የወንጌል መንግድ በትክክለኛው ጐደና እንድንቆይ ማድረጉን በማወቅ ለሌሎች ሰዎች ማካፈል ያስፈልጋል፡፡ ባቡር በሃዲድ እንደሚቆየው ሁሉ እኛንም እንደዚያው በትክክለኛው መንገድ እንድንቆይ ይረዳናል፡፡ ባቡር ከሐዲዱ ወጥቶ ሲሄድ አይተህ ታውቃለህ) መንገድ ይዞ መሮጥ አቅጫጫን አውቆ ለመሄድ ይጠቅማል፡፡
--------- ን አቅጣጫ ማወቁ እንደረዳው ሁሉ የወንጌልን መንገድ ማወቅ እኛንም ይጠቅመናል፡፡ (በክፍት ቦታው ላይ ድራማውን የሰራው ሰው ስም ይገባል) ስለ ኢየሱስ ለጓደኞቻችን በምንናገርበት ጊዜ ግራ እንዳንጋባ ከየት እንደምንጀምር፣ ወዴት መሄድ እንደምንፈልግ ለመረዳት ያስችለናል፡፡ አቅጣጫውን ካወቅን ወዴት እንደምንሄድ ከገባን ከእኛ ውጪ ሌላ ሰውም መረዳት እንችላለን፡፡

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፉ ላይ ያለውን መስራት፡፡ የወንጌል መንገድ ገጽ 1 እና 2
- በጋራ መጸለይ

የቤት ስራ

- የመጽሐፍ ማስታወሻ (የተግባር የቤት ስራ መጽሐፍ)

የመጽሐፍ ማስታወሻውን እንዴት የምስራች ቃሉን ለጓደኞቻችን እንደምንናገርበት ማሳየት፡፡ የተማሩትን ለሌሎች መንገር (የመጽሐፍ ማስታወሻ)

ፀሎት
ኢየሱስ መንገዱን ስላሳየኸን እናመሰግንሃለን አሜን፡፡

የመምህሩ ማስታወሻ፡
ልጆችን የወንጌል ጐዳናን እንዲያጠኑ በማገዝ ወቅት በቅንፍ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የሚል ቃል በመጨመር ልጆች የተወሰደው ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

ምዕራፍ 4፡ የምስራች ቃል



የትምህርት ግቦች

- ልጆች ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና ምን እንደሰራ ይማራሉ።
- ልጆች የምስራቹን ቃል በእጅ ከሚሰራው እንቅስቃሴ ቃል ያጠናሉ።
- ዝግጁ ከሆኑ ለኢየሱስ በመስጠት እና በመመለስ ዝግጁነታቸውን ያሳያሉ።
- ልጆች የተማሩትን እንዲያካፍሉ ይበረታታሉ።

እንኳን ደህና መጣችሁ፣ ፀሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

አዲሱ ጓደኛ (አሻንጉሊትም ሊሆን ይችላል) ታመመ።

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት መለከስና የቤት ስራቸውን እንዴት የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት መጠየቅ።

የማስተማሪያ ነጥቦች

ውይይት፡ ወንጌል

ልጆቹ ከታች ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ ቃላት እና አባባሎች መፃፍ።

ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ምን ማድረግ አለብን?

ውይይቱ ይቀጥል

ወንጌል የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትኛውን ክፍል ነው ወንጌል ብለን የምንጠቅሰው?
የወንጌል የምስራች ድምጽ ምንድን ነው?
መዳን ማለት ምን ማለት ነው?
ለምንድን ነው የዳንነው?

አስተዋውቅ፡ የምስራቹ ቃል

በቀላሉ የወንጌልን መሠረታዊ መልዕክቱን ማካፈል እንችላለን። ይህም የምስራች ቃል ይባላል። የምስራች ቃል የወንጌልን መሠረታዊ እውነቶች ያካተተ ነው። ይኸውም የዘላለምን ህይወት ለማግኘት ምን ማወቅ እንዳለብን ነው። ይህ የምስራቹን ቃል ለጓደኞቻችን ወንጌልን ለመንገር ቀላል መንገድ ነው።

መሸምደድ፡ የምስራች ቃል

ከእጅ ልምምዱ/ ተግባሩ አንድ ላይ የምስራቹ ቃል ይሸመደዳል/ ይጠናል፡፡ ይህም ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረው የወንጌል መንገድ ክፍል ነው፡፡

ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡
ከሰማይ ወደ ምድር መጣ፡፡
የጽድቅ ህይወት ኖረ፡፡
ለኛ ኃጢአት ሲል በመስቀል ላይ ሞተ፡፡
ከሞት ተነስቶ በአብ ቀን ተቀምጦ፡፡
የዘለአለም ህይወት እንድናገኝ ይጋብዘናል፡፡

‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት
እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር
አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ
ዓለምን እንዲሁ ወዷልና፡፡›› (ዮሐ 3፡16)

ስድስት የምስራች ቃል የማስታወቂያ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረውን የወንጌል መንገድ ልጆች እንዲያጠኑት መርዳት፡፡

ዮሐ 3፡16ን ማብራራት እና መወያየት፡፡ ጥቅሶችን ለማስጠናት መዝሙር ወይም ጨዋታዎች ን የመሰሉ መግባቢያ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል፡፡

ድራማ፡ አዲሱ ጓደኛ የምስራች ቃል ሰማ/ች

ለ_____(የአዲሱ ጓደኛ ስም) የምስራቹን ቃል ሰምቶ መንግስተ ሰማይ ይገባ ዘንድ ምን እንንገረው?

_____ አንተ ጥሩ ጓደኛ ነህ ስለዚህ አንድ ደስ የሚል ዜና ልነግርህ እፈልጋለሁ፡፡ መጽ ሐጽ ቅዱስ ሳነብ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ እና ከሰማይ ወደ ምድር እንደመጣ ተረድቻ ለሁ፡፡ የጽድቅን ህይወት ኖሮ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ አሁን በመንግስተ ሰማይ ለኛ የዘላለም ህይወት ለመስጠት እየጋበዘን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹በእርሱ የሚያም ን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዷልና››

_____ አሁን ያካፈልኩህን ነገር እስኪ አስብ፡፡

የጥንብ አንሳ አደን

በአካባቢያችን የሚገኘውን ማንኛውም ቁሳቁስ (ነገር) እንዴት ወንጌልን ለመስበክ እንደ ምንጠቀምበት ማወቅ አለብን፡፡

መምህራን ተራ እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ቁስ በምሳሌነት ያሳያል፡፡ ይህ ሚጠቅመ ው በማንኛውም ቁስ ወንጌልን መናገር እንደሚቻል ማሳየት ነው፡፡

ምሳሌ :

ውሃን ተመልከቱ ያዝናናል፣ ንጹህ ያደርገናል፣ በህይወት እንድንኖርም ይረዳናል፡፡ ይህ የኢየሱስ ን የህይወት ውሃን ለመስጠት ከኃጢአታችን ለማንፃት እና የዘላለም ህይወት እንድናገኝ ያደረገውን ግብዣ ያስታውሰኛል፡፡

ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዶ የጽድቅን ህይወት ኖሮ ...

የቀልድ ድርጊቶች ማለት በክፍል ውስጥ ወይም በህንፃ ላይ በመዘዋወር ወንልጌን ለመናገር የሚያስችል ቁስ መፈለግ ነው፡፡

ውይይት እና ሽምደዳ፡ ምላሽ

ወንጌልን ለአንድ ሰው በምንመሰክርበት ወቅት ምላሽ እንዲሰጥ እድል ልንሰጠው ወይም ልንሰጣት ይገባል፡፡ ይህን በመጠየቅ ማድረግ እንችላለን፡፡

የምለው ነገር ገብቶሃል?

ኢየሱስን ስለ ኃጢአትህ ይቅርታ መጠየቅ እና
የተዘጋጀልህን የዘላለም ህይወት
መቀበል ትፈልጋለህ?

ይህ ማለት ኢየሱስን እመነው፡፡ ከኃጢአትህ
ተመለስ ኢየሱስን ተከታተለው፡፡

ይህን ነው የምትፈልገው) ስለዚህ አብረን መጸለይ እንችላለን፡፡

‹‹ጌታ ኢየሱስ ሆይ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ
የህይወቴ ጌታ እና አዳኝ ሁን አሜን!››

‹‹በእኔ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው፡፡›› (ዮሐ 6፡47)

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰቦች በሰላም መጡ!

ማብራሪያ

(አበባ መትከያ ማሰሮ፡ ዘር እና ውሃ ወይም በስዕል መጠቀም)

አንድ ሰው ኢየሱስን ብቻ በሚያምንበት ወቅት ስራው የመንፈስ ቅዱስ እንጂ የኛ አለመሆኑን ልናስታውስ ይገባል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር አንዱ ዘር ይዘራል ሌላው ደግሞ ያጠጣል፡፡ ሁላ ችንም ፍሬውን ለመብላት ብንጓጓም መትከል እና ማጠጣትም በእግዚአብሔር አይን እኩል ዋጋ አለው፡፡ እኛ በተናገርን ጊዜ ግለሰቡ ጌታን ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆን በዚያ ልናዝን አይገባም፡ ፡ በመናገራችን በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ጠንካራ መሆን አለበት (መትከልና ማጠጣት)

ልጆች የምስራቹን ቃል እርስ በእርሳቸው እና ለአዲሱ ጓደኛቸው እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ አን ድ ልጅ እንደ አዲሱ ጓደኛ ሲሆን ሌላው ደግሞ እንደመስካሪ ይሁን ጊዘ ካለ ተቀያይረው ደግ ሞ ይለማመዱ፡፡

የቡድን ሰዓት

- በየምስራች ቃል ገጽ 3 እና 4 ላይ የሚገኘውን የተግባው ስራ አጠናቅ፡፡
- በጋራ መጸለይ

የቤት ስራ

<u>የቤት ስራ (የተግባር መጽሐፍ የቤት ስራ ገፆች)</u>

- የምስራቹን ቃል ተለጣጣፊ ወረቀት በካርዱ ላይ አስቀምጥ፡፡
- በትንሽ ሳጥን ቴሌቭዥን በመስራት የምስራቹን ቃል በውስጡ በማድረግ እያሸከረከር ክ ወንጌልን መናገር ይቻላል፡፡
- የምስራቹን ቃል ቁራጭ ቁረጡ ለጥፉት ወይም የቁራጩን መጨረሻዎች በማጋጠም እጃችሁ ላይ አድርጉት። .

ፀሎት

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ለእኔ ኃጢአት ስለሞትክልኝ አመሰግንሃለሁ አሜን!

የመምህሩ ማስታወሻ፡

የምስራቹን ቃል ብዙ ልጆች ላይረዱት (ሙሉ በሙሉ) ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምዕራፍ 11 ከተማሩ በኋላ የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፡፡

የምስራች ቃሉን ስንናገር የተለያየ አይነት ምላሾችን እናገኛለን፡፡ የተለያዩ አይነት ምላሾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. አንዳንድ ልጆች አስቀድመው ተረድተው እና ምላሽ ሰጥተው ሊሆን ይችላል፡፡
2. አንዳንድ ልጆች እንዳልገባቸው ሊናገሩ ይችላሉ፡፡
3. አንዳንድ ልጆች ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡
4. አንዳንድ ልጆች ዝግጁ እንዳልሆኑ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡
5. አንዳንድ ልጆች ደግሞ ዝግጁ መሆናቸውን ሊናገሩ ይችላሉ፡፡

ልጆች የተማሩት እና የሚሰጡት ምላሽ በእግዚአብሔር አሳሳቢነት (እውቀት) መሄዱ ን እንዲያውቁ እድል ልንሰጣቸው ይገባል፡፡

ልጆች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲገልጹ እድል ሊያገኙ ይገባል፡፡ ነገር ግን እንደተጫናችኋቸው ሊያስቡ በፍጹም አይገባም፡፡

- ልጆች በውሳኔ ወቅት ጫና ያደረባቸው መስሎ ሊሰማቸው አይገባም፡፡ ያለ ብስለ ት የሆነ ውሳኔ ሊወስኑ ስለሚችሉ ይሄ ደግሞ በህይወታቸው ውስጥ አሉታዊ ተጽዕ ኖ ስለሚኖረው ይህ እንዳይፈጠር መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡
- መንፈስ ቅዱስ በልጁ/ ልጅቷ ህይወት ውስጥ እንዲሰራ ሁሉም ንቁ መሆን ያስፈ ልጋል፡ ልጆቹ ኢየሱስን እንደግል አዳኝ ሲቀበሉ የመንፈስ ቅዱስ እንጂ የእኛ ስራ አለመሆኑን ማብራራትና ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡
- በመሰከርንለት ጊዜ ኢየሱስን ለማመን ፍቃደኛ ካልሆነ በዚህ ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም፡፡ መጀመሪያ ሊያስቡበት ስለሚፈልጉ ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን እኛ በመመስከራችን በእግዚአብሔር ያለንን እምነት ያሳያል፡፡

መልሶችን እንዴት መቀበል እንዳለብን የሚያስረዳውን መርህ በደንብ ለመረ ዳት ምዕራፍ 11 ላይ ያለውን እንዴት ምላሾችን በውጤታማነት ማስተናገድ እንደምንችል የሚለውን ማመሳከር ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ 5፡ እንነጋገር



የትምህርት ግቦች

- ልጆች የህይወት ምስክርነታቸውን በማካፈል ግንኙነትን መመስረት መቻል አለባቸው።።
- ልጆች የሁለቱን ጥያቄዎች አላማ በደንብ መረዳት እና የሚነግሩትንም ሰው መንፈሳዊ ደረጃ ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው።።
- ልጆች መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለም ህይወት እንዳገኘን እንደሚያረጋግጥልን ሊያውቁ ይገባል።።

እንኳን ደህና መጣችሁ፣ ፀሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

ቡድን መሪው እንደ ሐኪም ይለብሳል።.

ክለሳ

የባለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት ከከለስክ በኋላ ልጆች የምስራች ቃል የያዘ ወረቀታቸውን እንዴት ወንጌል ለመናገር እንደተጠቀሙበት ጠይቅ።።

ለሌሎች የተማሩትን ለመንገር የቤት ስራውን መጠቀም

የማስተማሪያ ነጥቦች

ውይይት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ግንኙነት ማዳበር

በምዕራፍ 2 ላይ ስለሌሎች በደንብ ለማወቅ የሚሉትን በደንብ መስማት እንዳለብን ተምረናል።። አሁን ደግሞ ግንኙነትን ለማዳበር እንዴት ጥያቄዎችን እንደምንጠይቅ እንማራለን።። ለመጀመር ያህል ወደ ሌላ ጥያቄ የሚመሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም የግል ምልከታ ወይም አስተያየት በመስጠት መጀመር ይቻላል።።

ለምሳሌ፡

- ስለ እግዚአብሔር አስበህ ቃውቃለህ? እግዚአብሔር ምን ይመስላላ ብለህ አሰብክ?
- የፈጠረህ እግዚአብሔር እንደሚወድህ ታውቃለህ?
- ስለ እሱ የበለጠ ማወቅ ትፈልጋለህ?
- እግዚአብሔር እንድትወደው እንደሚፈልግ ታውቃለህ?
- ኢየሱስ ማን ይመስልሀል?
- መልካም ዜና ልነግርህ እችላለሁ?

ሰዎችን ማስቀየም ስለማያስፈልግ እንደሚከተሉት አይነት ጥያቄዎችን አትጠይቅ

- ድነሃል? ክርስቲያን ነህ?

ውይይት፡ የራስህን ታሪክ የመናገር ሃይል

የምትናገረውን ታሪክ አስደሳች የሚያደርገው ታሪኩ ስለራስህ ስለሚናገር ነው። ታሪክህን ማካፈል ማለት በአይንህ ያየኸውን፣ በራስህ ራይ የደረሰውን፣ በትክክል እውነት የሆነውን ነገር መናገር ማለት ነው። ታሪክህ የራስህ ምስክርነትም ሊባል ይችላል። ምስክርነት ማለት በትክክል ያየኸውን ወይም እውነትነቱ በእርግጥ የቃወቀን ነገር መናገር ማለት ነው። የአንተ የግል ታሪክ ማለት ኢየሱስ በህይወትህ ውስጥ ያመጣውን ልዩነት (ለውጥ) መናገር ነው። ይህ መንፈሳዊ ንግግሮችን ለመጀመር እንደ መግቢያ ሊሆን ይችላል።

ማብራሪያ፡ ፊደል

ለልጆች ትንሽ ፊደል አቅምሳቸው። ታሪክህም ልክ እንደ ፊደል ስለ ታሪክህ ለመስማት እንዲጠሙ እና እንዲጓጉ ያደርጋል። ታሪኩ ኢየሱስ በህይወትህ ውስጥ ምን እንዳደረገ ለመስማት ያጓጓቸዋል።

ሽምደዳ፡ መናገር እና ምስክርነት

ስለ እግዚአብሔር አስበህ ታውቃለህ) እስቲ ንገረኝ።
እግዚአብሔር አንድ ቀን አብረነው በመንግስተ ሰማያት እንድንሆን ይፈልጋል።

የመምህሩ ማስታወሻ፡

ይህን ምዕራፍ ከፋፍሎ ለማስተማር ትፈልግ ይሆናል።

በተለየ ልጆቹ ምስክርነታቸውን ለመናገር በመንፈሳዊ ነገር ዝግጁ ከሆኑ እንደዚያ የ ምታደርግ ከሆነ ይህን አቁምና በገጽ 29 እና 30 የመምህሩ መጽሐፍ እና በገጽ 6 እ ና 7 የተግባር መጽሐፍ ላይ ያለውን የቡድን ስራ አሰራ።

ሁለቱ ጥያቄዎች : ምርመራ

እንዴት ንግግር እንደምትጀምሩ፣ እንዴት ታሪካችሁን መናገር እንደምትችሉ ተምራችኋል። ሌሎችም ታሪካቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት ያስፈልጋል።

አሁን ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማያት መግባታቸውን እርግጠኛ መሆናቸውን የምንጠይቅበትን ሁለት አስፈላጊ ጥያቄዎች እንማራለን። እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉም ሰው ሊመልሳቸው የሚገቡ ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው።

በምንታመምበት ጊዜ በሽታችንን ለማወቅ (ለመርመር) ሐኪም ጥያቄ ይጠይቀናል። በተጨማሪም ምርመራ እና የህክምና ሙከራም ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መከራዎቹን ብቻ ማድረግ በቂ አይደለም። ሙከራዎቹን ማንበብ እና መተርጎም አስፈላጊ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ እኛም ጥያቄ ስንጠይቅ መልሱን መረዳት መቻል አለብን። በመጀመሪያ ሁለቱን ጥያቄዎች እንማር።

መሸምደድ፡ ሁለት ጥያቄዎች

አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?
አንድ ቀን በመንግስተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር
እንደምትሆን በእርግጠኝነት ታውቃለህ?
እግዚአብሔር ለምንድን ነው ወደ መንግስተ
ሰማይ የማስገባህ?
ብሎ ቢጠይቅ ምን ትላለህ?

ውይይት፡ የሁለት ጥያቄዎች ምላሾች

የመጀመሪያ ጥያቄ

የመጀመሪያውን ጥያቄ እንጠይቅ፡ አንድ ቀን በመግስተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምትሆን በእር ግጠኝነት ታውቃለህን?
ምን አይነት መልስ የምታገኝ ይመስልሃል?

- ☐ አዎን
- ☐ አይደለም
- ☐ እርግጠኛ አይደለሁም ወይም ተስፋ አደርጋለሁ

ሁለተኛ ጥያቄ

ሁለተኛውን ጥያቄ ብንጠይቅስ፡ እግዚአብሔር ለምንድን ነው ወደ መንግስተ ሰማይ የማስገባህ? ብሎ ብጠይቅም ምን ትላለህ?

ግለሰቡ ኢየሱስን እንደግል አዳኙ የተቀበለ ከሆነ ምን አይነት መልስ ሊሰጥ ይችላል?

- ☐ ኢየሱስ እንዴት ስለ ኃጢአቱ እንደሞተ መናገር::
- ☐ ኢየሱስ እንዴት አዳኝና ጌታ እንደሆነ መናገር::
- ☐ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ ያመኑት ለዘላለም ህይወት ሲሉ ነው፡፡

በኢየሱስ የማያምን ግለሰብ ለሁለተኛው ጥያቄ ምን አይነት መልስ ሊሰጥ ይችላል?

- ☐ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ያደረሱትን መልካም ስራ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡
- ☐ ጥሩ ህይወት ለመኖር መሞከር::
- ☐ ቤተክርስቲያን መሄድ ::

የሚቀጥለው ድራማ ልትሰሙት የምትችሉትን መልሶች ሊያብራራ ይችላል፡፡ የሚሰጡ ትን መልሶች መመርመር (መረዳት) ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፡

- ☐ ስለ ኢየሱስ የምስራች ቃል መስማት ትፈለጋለህ?
- ☐ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ማስተማመኛ ትፈለጋለህ?
- ☐ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት እርግጠኛ ናቸው?

ድራማ ዶ/ር ሳኦል

ይህ ድራማ መረዳት የሚያስችሉት ሁለት ጥያቄዎችን እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡ አንዱ የቡድን መሪ የዶ/ር ሳኦልን ገፀ ባህርይ ተላብሶ ይጫወታል፡፡ ነርስ የሚሆን አንድ ልጅ እና ታካሚዎች የሚሆኑ አራት ልጆች ምረጡ፡፡ ታካሚዎቹ በሚሰ ጡዋቸው ምላሾች በኢየሱስ የሚያምኑ መሆን አለመሆናቸውን መለየት ችትላላችሁ፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ምርመራውን ከመጀመራችን በፊት የጭንቀት ሙከራ እናደርጋለን፡፡ የሮሜ 6፡23 መዝሙር እንደ ጭንቀት መሞከሪያ አብረን እንላለን፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ወደ ፊት በመምጣት ከተማሪዎች ፊት የሚገኘው ወንበር ላይ ተቀምጠ ነርሷን አንደኛውን ታካሚውን እንድታስገባለት ይጠይቃል::

ታካሚ 1 /የመጀመሪያ ታካሚ/

ነርሷ የመጀመሪያውን ታካሚ ወደ ዶክተሩ እንዲገባ ትነግረዋለች፡፡ ታካሚው ገብቶ ከዶ/ር ፊት ያለው ክፍት ወንበር ላይ ይቀመጣል፡፡ ታካሚ 1 ጠንካራ እና ጤነኛ ነው፡፡ የመጣው ጤንነቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በኢየሱስ አምኖ ስለመዳኑ እርግጠኛ ነው፡፡

ዶ/ር ሳኦል ለዚህ ምርመራ (የማረጋገጫ) ስለመጣህ አመሰግንሃለሁ፡፡ ሁለት አጫጭር ጥያቄዎ ችን በመጠየቅ እጀምራለሁ፡፡ የመጀመሪያው አንድ ቀን መንግስተ ሰማይ ከእግዚአ ብሔር ጋር እንደምትሆን በእርግጠኝነት ታውቃለህ) (ዶ/ር ሳኦል ጥያቄዎቹን እየጠ የቀ ምርመራውን በበሽተኛው ላይ ያካሂድ ነበር፡፡ የልብ ምት፣ ግንባሩን በመንካት ትኩሳት እና የልብ ትርታውን መስማት የመሳሰሉትን)

ታካሚ 1 አዎን /የመጀመሪያ ታካሚ/

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ፡፡ ሁለተኛው ጥያቄ እግዚአብሔር በምንድነው ወደ መንግስተ ሰማይ የማስገባህ? ብሎ ቢጠይቅህ ምን ትላለህ?

ታካሚ 1፡ ይወደኛል፣ ለኔ ሲል በመስቀል ሞቷል፡፡ኢየሱስ ብቻውን ከኃጢአት ቅጣት ሊያድነኝ ይችላል፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ በጣም ጥሩ እንደዚህ ስለተሰማህ ደስተኛ ነኝ፡፡ በኋላ በደንብ እናወራለን፡ ፡ አሁን ወደ መቆያው ቦታ ተቀምጠህ ጠብቀኝ፡፡

<u>የቡድን ውይይት፡ ታካሚ 1 ወደ መንግስተ ሰማይ እገባለሁ ብሏል?</u>

ታካሚ 2 /ሁለተኛ ታካሚ/

ነርሷ ሁለተኛውን ታካሚ ወደ ዶ/ር ሳኦል ታስገባለች፡፡ ሁለተኛው ታካሚ የተረጋጋ አይመስ ልም ደረቱን በእጁ ይዞ ወደ ዶ/ር ክፍል ገባ፡፡ ሁለተኛው ታካሚ ስለ መዳኑ እርግጠኛ አይደ ለም፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ወደዚህ ለምርመራ በመምጣትህ አመሰግናለሁ፡፡ ሁለት እጭር ጥያቄዎችን በመ ጠየቅ እጀምራለሁ፡፡ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ምትሆን በእርግጠኝነት ታውቃለህ? (ጥያቄዎች ከመጠየቅ ጐን ለጐን ዶ/ር ሳኦል ምርመራውን ያካሂዳል)

ታካሚ 2፡ አይደለሁም፣ እርግጠኛ አይደለሁም

ዶ/ር ሳኦል፡ እ እ... ጥሩ ሁለተኛው ጥያቄ እግዚአብሔር ለምን ወደ መንግስተ ሰማይ አስገባህ ለሁ? ብሎ ቢጠይቅህ ምን ትላለህ?

ታካሚ 2፡ አላውቅም መንግስተ ሰማይ ላመነበት የሚያስችል ጥሩነት አለኝ ብዬ አላስብም እኔ

ክፉ ሰው ነኝ፡፡ታናሽ እህቴን እቆታለሁ ወላጆቼ አንድአንድ ጊዜም ወላጆቼን አልታዘ

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ! ላንተ መልካም ዜና አለኝ፡፡ መንግስተ ሰማያት ነፃ ስጦታ ነው፡፡ መንግስተ ሰማይ አንተ ከሰራኸው ነገር ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ (ዶ/ር ሳኦል ምርመራውን ያቆማል? በኋላ የበለጠ እንነጋገራለን ለአሁኑ እንግዳ መቀበያው ጋር ቁጭ ብለህ ጠብቀኝ፡፡

የቡድን ውይይት:- ሁለተኛው ታካሚ ወደ መንግስተ ሰማይ እገባለሁ አለ? በማን ነው የሚያ ምነው?

ታካሚ 3

ነርሷ ሶስተኛውን ታካሚ ወደ ዶ/ር ሳኦል ታስገባዋለች፡፡ ሶስተኛው ታካሚ የሐዘን ስሜት ይ ታይበታል አልተረጋጋም አንገቱን አቀርቅሮአል፡፡ ኢየሱስ እንደሚያድን ያምናል ማረጋገጫ ግን ይፈልጋል፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ለምርመራ በመምጣትህ አመሰግናለሁ፡፡ ሁለት አጫጭር ጥያቄዎችን በመጠየቅ እጀምራለሁ፡፡ የመጀመሪያው አንድ ቀን መንግስተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር እን ደምትሆን በእርግጠኝነት ታውቃለህ) (ዶ/ር ሳኦል ከጥያቄው ጐን ለግን በሽተኛው ን ይመረምራል)

ታካሚ 3፡ እኔንጃ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ ሁለተኛው ጥያቄ እግዚአብሔር ለምን ወደ መንግስተ ሰማይ አስገባሃለሁ? ብሎ ቢጠይቅህ ምን ብለህ ትመልሳለህ?

ታካሚ 3፡ ኢየሱስን እወደዋልለሁ፡፡ ለኃጢአቴም ይቅር እንዲለኝ እለምነዋለሁ፡፡ ወደ መንግስ ተ ሰማይ መግባት እፈልጋለሁ፡፡ ግን እንደምገባ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ በጣም ጥሩ ዜና አለኝ! አየህ መንግስተ ሰማይ በነፃ የሚሰጥ ስጦታ ነው እንጂ በስራ የምታገኘው ወይም ስለተገባህ የሚሆን ነገር አይደለም፡፡ በኋላ በደንብ እናወ ራለን አሁን መቆያው ጋር ቁጭ ብለህ ጠብቀኝ፡፡

<u>የ</u>ቡድን ውይይት፡ ሶስተኛው ታካሚ ወደ መንግስተ ሰማይ እገባለሁ ብሎአል) በማንስ ነው የሚያምነው?

ታካሚ 4 /4ኛ ታካሚ/

ነርሷ አራተኛውን ታካሚ ሐኪሙ ሊያናግረው እንደሚችል ተናግራ ታስገባዋለች፡፡ አራተኛው ታካሚ ከልክ ያለፈ በራስ መተማመን የነበረው እብሪተኛ ነው፡፡ የሰራቸው መልካም ስራዎች መንግስተ ሰማይ ሊያስገባው እንደሚችል ያምናል፡፡ በቂ ጥሩ ስራ ከሰራ እግዚአብሔር ወደ መ ንግስተ ሰማይ ሊያስገባው እንደሚችል ያምናል፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ለምርመራ በመምጣትህ አመሰግናለሁ፡፡ ምርመራውን የምጀምረው ሁለት አጫጭር ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው፡፡ የመጀመሪያ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያተ ከእግዚአብሔር ጋር ልትሆን እንደምትችል በእርግጠኝነት ታውቃለህ?(ዶ/ር ሳኦል ከጥያቄው ጎን ለጎን በሽተኛውን አካላዊ ጤና ይመረምራል)

ታካሚ 4፡ አዎ በጣም እርግጠኛ ነኝ፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ ሁለተኛው ጥያቄ እግዚአብሔር ለምንድነው ወደ መንግስተ ሰማያት የማስገባህ? ቢልህ ምን ብለህ ትመልሳለህ?

ታካሚ 4፡ ምክንያቱም እኔ ጥሩ ሰው ነኝ ወደ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ እሄዳለሁ፣ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ለሰዎች አደርጋለሁ አንደ አንዳንድ ሰዎች ክፉ እና መጥፎ ስራዎችን አልሰራም፡፡

ዶ/ር ሳኦል፡ ጥሩ ለአንተ መልካም ዜና አለኝ! መንግስተ ሰማይ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ በስራህ ወይ ም ስለሚገባህ የምታገኘው አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ነው፡፡ በኋላ በሰ ፊው እንነጋገራለን እስከዛ በመቆያ ቦታ ቁጭ ብለህ ጠብቀኝ፡፡

የቡድን ውይይት፡ አራተኛው ታካሚ ወደ መንግስተ ሰማይ እገባለሁ አለ?

ክለሳ፡ የታካሚዎች ምላሽ

ልጆች በታካሚዎቹ መልሶች ላይ የሰጧቸውን መላ ምቶች እንደገና በማየት አራቱ ታካሚዎች የሰጡትን ምላሽ አጢን፡፡ የልጆቹን መልሶች ከመረመርክ በኋላ አራቱ ታካሚዎች እንደሚያስ ፈልጋቸው ጠይቅ፡፡

- የመጀመሪያው ታካሚ ያመነው ኢየሱስን ሲሆን ለመንፈሳዊ እድገቱ ማበረታቻ እና የፀሎት ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡
- ሁለተኛው ታካሚ በኢየሱስ አያምንም ስለዚህ ስለ ወንጌል መስማትና የዘላለም ህይወትን ማግኘት አለበት፡፡
- ሶስተኛው ታካሚ በኢየሱስ ያምናል ነገር ግን ስለ ዘላለም ህይወት እርግጠኛ ስላልሆነ ስለ ወንጌል ሊሰማ ይገባል፡፡
- አራተኛው ታካሚ በኢየሱስ አያምንም፡፡ ትክክል ባልሆኑ ነገሮች ስለሚያምን ወንጌልን መስማት እና የዘላለም ህይወትን ማግኘት አለበት፡፡

የመምህሩ ማስታወሻ፡

ማንም ሰው ለጌታ ማድረግ ስላለበት ነገር ልጆች ዳኝነት መስጠት እንደሌለባቸው ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ መንግስተ ሰማይ ማን ሊገባ እንደሚችል የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነውና፡፡ እኛ የምናደርገው ግለሰቡ መንግስተ ሰማይ መግባቱን በእርግጠኝነት ያውቃል ወይስ አያውቅም እና በማን እንደሚያምን/ እንደማያምን መለየት ነው፡፡

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን ተግባራት ማከናወን፡፡ ገጽ 5፣ 6 እና 7
- የቡድን መሪዎች በየራሳቸው ትንንሽ ቡድኖች የራሳቸውን ታሪክ በመናገር ልጆቹ የራ ሳቸውን ታሪክ እንዲጽፉ ማበረታታት አለባቸው፡፡ የፃፉትንም ከቡድን መሪያቸው እና ከሌሎች ልጆች ጋር እንዲከፋፈሉት ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡
- በጋራ መጸለይ

እነዚህ ኢየሱስ እንዴት በህይወታችን ለውጥ እንደሚያመጣ ማሳያዎች ናቸው።

ከ / ለ

ስጋት	→	ሰላም	ደካማ	→	ጠንካራ
መፍራት	→	አለመፍራት	አለመታዘዝ	→	መታዘዝ
ብቸኝነት	→	ጓደኝነት	ያልተረጋጋ	→	የተረጋጋ
ሃዘን	→	ደስታ	የተጠላ	→	የተወደደ
መገፋት	→	ተቀባይነት ማግኘት			

ጓደኞቻችንን በይበልጥ ማወቅ እንፈልጋለን። ግንኙነቶችን ለማዳበር ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ታሪኮችን በመንገር እናዳብረዋለን። ይህ ስለ ኢየሱስ ብዙ ለማወቅ እንዲጓጉ ሊያደርጋቸው ይቻላል።

የቤት ስራ

- የሁለት ጥያቄዎች ሃብል ወይም ባጅ

ልጆች አንገት ሐብል ወይም በባጅ መልክ በወረቀት ላይ እንዲሰሩ በማድረግ የጥያቄ ምልክት በማድረግ በአንገታቸው ላይ እንደ ሪባን ወይም እንደ ባጅ እንዲያደርጉት አድርግ።

እነዚህን ሃብሎች ወይም ባጆች በመጠቀም ለጓደኞቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው ስለ ግል ታሪኮቻቸውን እንዲነግሩን ሁለቱን ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት።

ፀሎት

ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተን በማወቃችን እና የአንተ በመሆናችን ወደ መንግስት ሰማይ እንድንገባ ስለረዳኸን እናመሰግንሃለን። ለሌሎችም ስለ አንተ እንድንናገር እርዳን አሜን!



የትምህርት ግቦች

- ልጆች ስለ ፀጋና መንግስተ ሰማይ (ነፃ ስጦታ መሆኑን (የዘላለም ህይወት) መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ይኖራቸዋል፡፡
- ልጆች የመንግስተ ሰማይ ክፍልን በወንጌል ጎዳና ትምህርት ውስጥ ከነእጅ ምልክቱ ያ ውቃሉ፡፡
- ልጆች መንግስተ ሰማይ ምን እንደሚመስል ሃሳብ ይኖራቸዋል፡፡

እንኳን ደህና መጡ፣ ፀሎት፣ ምስጋናና መዝሙር

አዲሱ ጓደኛ (አሻንጉሊት ወይም ሰው ሊሆን ይችላል) ከስጦታ ጋር አብሮ ይቀመጣል (ይሰጠዋል)፡፡

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ በመከለስ ልጆች እንዴት የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት መጠየቅ፡፡

የማስተማሪያ ነጥቦች

ድራማ፡ የሶስት ስጦታዎች ቀልድ

ይህንን ቀልድ የወንጌል መንገድ መንግስተ ሰማይ የትምህርት ክፍልን ለማስተዋወቅ መጠቀም፡፡

በእያንዳንዱ የስጦታ ሳጥን ላይ እንዲህ የሚል ጽሁፍ አድርግ፡፡

የመጀመሪያ ስጦታ፡ መንግስተ ሰማይ በስራችን የሚገባን አይደለም፡፡
ሁለተኛ ስጦታ፡ መንግስተ ሰማይ የሚገባን አይደለም፡፡
ሶስተኛ ስጦታ፡ መንግስተ ሰማይ ነፃ ነው፡፡

<u>የመጀመሪያ ስጦታ (ሰርተን የምናገኘው ስጦታ)</u>፡ አንድ ልጅ ተነስቶ ስጦታ ልሰጥህ እፈልጋ ለሁ እንድትወስደው ከፈለክ በአንድ እግርህ አስር ጊዜ ዝለል ይበለው፡፡ በአንድ እግሩ አስር ጊዜ ከዘለለ በኋላ አመስግናችሁ ስጦታውን ስለለፋበት ወይም ስለሰራ እንዳገኘ በመናገር ስጡት፡

<u>ሁለተኛው ስጦታ (የሚገባው ስጦታ)</u>፡ ሁለተኛው ልጅ በመጥራት ትከሻውን መታ መታ በማ ድረግ ስጠታውን በመስጠት እና ስለ እርሱ መልካም ነገሮችን መናገር፡፡ ‹‹አንተ በጣም ጥሩ ተማሪ ነህ አታረፍድም በሰዓትህ ነው የምትመጣው፣ የዋህ ልጅ ነህ ፡፡ ይህ ስጦታ ይገባሃል፡፡›› ለልጁ ስጦታው የተሰጠው ስለሚገባው መሆኑን አጽንኦት ሰጥተህ አሳይ፡፡

<u>ሶስተኛ ስጦታ (ነፃ ስጦታ)</u> በመጨረሻ ላይ አንዲት ልጅ እንድትመጣ በማድረግ ስጦታውን ከሰጠህ በኋላ ስጦታ ስትቀበይ ይህን ለማግኘት ምንም መስራት አይጠበቅብሽም የሰጠሁሽም ስለሚገባሽ አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህን የሰጠሁሽ ስለምወድሽ ነው በነፃ፡፡

ውይይት፡ የሶስቱ ስጦታዎች ቀልድ/ ጨዋታ

እነኚህ ሶስት ስጦታዎች የተሰጡባቸው የተለያዩ መንገዶች ምንድን ናቸው?

ለምን ሁሉም ነፃ አልሆኑም) ለምን?

የእውነት ነፃ ስጦታ የነበረው የትኛው ነው?

መንግስተ ሰማያት ነፃ ስጦታ ነው፡፡ በስራ ወይም ስለተገባን የምናገኘው አይደለም፡፡

ታሪክ፡ የጓደኛ ስጠታ

በጣም የቅርብ ጓደኛዬ በጣም ውድ ስጦታ ሰጠኝ እንደ_____ አይነት፡፡ ለመክፈል ወይም በስራ ለመለወጥ ብሞክር ስጦታ መሆኑ ይቀራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መንግስተ ሰማይ ለመግባት መስራት ወይም እንዲገባን መሆን የለብንም ምክንያቱም መንግስተ ሰማያት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ነው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝሙር፡

ኤፌሶን 2፡8 እና 9

ኤፌሶን 2፡8 እና 9ን በማንበብ ኤፌሶ ን 2፡8 እንደ መግባቢያ መዝሙር አስ ጠና፡፡

መንግስተ ሰማይ መልካም ቦታ ናት
እዚያ ለመድረስ ፀጋ መኖር አለበት
እምነት የመግቢያው መንገድ ነው
ምንም ብንሰራ የማናመጣው ይህንንም
ለመማር ጊዜው ገና ነው
ኤፌሶን 2፡8 ላይ ነው፡፡



ውይይት: መንግስተ ሰማይ

በተስፋ ለህፃናት ትምህርት ላይ ስለ መንግስተ ሰማያት ስናወራ የዘላለም ህይወት ነው የምና ወራው፡፡ የዘላለም ህይወት መንግስተ ሰማይ ከመግባት የበለጠ ነገር ነው፡፡ የዘላለም ህይወት ማለት ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር አሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም የሚቆይ ግንኙነት ማድረግ ማለት ነው፡፡ መንግስተ ሰማይ በጣም ወደር የማይገኝለት ቦታ ነው፡፡ ኢየሱስን እንደ ግል አዳ ኝ በማመን በመንግስተ ሰማይ የዘላለም ህይወትን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር ማሳለፍ ልቻላ ል፡፡

እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር በማለት የዘላለም ህይወት በመስጠት በመንግስተ ሰማይ አብረ ነው እንድንሆን በፀጋው አድርጓል፡፡ ፀጋ ማለት የማይገባንን በጣም መልካም ነገር በነፃ ማግኘ ት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግስተ ሰማይ ምን እንደሚል እንመልከታ...

እድሜያቸው ከፍ ያሉ ልጆች ስለ ሲኦል ሊጠይቁ ይችላሉ ለውይይት እንዲያመች ሁለት ቦታ በመክፈል አንደኛው ቡድን ስለ መንግስተ ሰማያት አንደኛው ቡድን ስለ ሲኦል እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ የተነጋገሩበት በድራማ፣ በስዕል ወይም በውይይት እንዲከፋፈሉ ማድረግ፡፡

የውይይት ቡድን

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግስተ ሰማያት ምን ይላል?

መንግስተ ሰማይ ምንድነው)	በመንግስተ ሰማይ የሌለው ምንድነው)
• እግዚአብሔር መንግስተ ሰማይ አለ (ራዕይ 33፡3)	• እንባ፣ ሃዘን ፣ ህመም
• መልአክት መንግስተ ሰማይ ይገኛሉ (ራዕይ 5፡11)	• ፀሃይ ወይም ጨረቃ፣ ምሽት ወይም ጨለማ
• መንገዶች ከወርቅ የተሰሩ ናቸው (ራዕይ 21፡21)	• ኃጢአት (እርግማን፣ ውሸት፣ ማታለል፣ ራስ ወዳድነት እና ሌሎችም)
• የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበር (ራዕይ 21፡23)	• ባህር (መለያ)
• ሁልጊዜ ብርሃን አለ፡፡ ብርሃኑም የእግዚአብሔር ክብር ነው (ራዕይ 21፡19-21)	• ሞት
• የበጉ የሆነው የህይወት መጽሐፍ መንግስተ ሰማያት ይገኛል (ራዕይ 21፡27) ስምህ እዚህ መጽሐፍ ላይ ተጽፏል)	• ለቅሶ (ራዕይ 21፡4)

2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሲኦል ምን ይላል (በምርጫ)

- ሲኦል በእውነትም አለ (ማቴዎስ 25፡41-46)
- እግዚአብሔር ለሰይጣን እና ለጭፍሮቹ ያዘጋጀው የቅጣት ቦታ ነው፡፡ በተጨማሪም ኃጢአታቸው ይቅር ያልተባሉ ሰዎች የሚገቡበት ቦታ ነው (ማቴ 25፡41)
- ከእግዚአብሔር የመለየት እና የስቃይ ቦታ ነው (ማቴ 25፡41)
- የስቃይና የቃጠሎ ቦታ ነው (ሉቃ 16፡23-24)
- ኢየሱስ ስለ ጨለማ ለቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት ተናግሯል (ማቴ 8፡12)
- ዮሐንስ ሁለተኛው ሞት ይለዋል (ራዕይ 21፡8)

የመጽሐፍ ቅዱስ ውይይት ሮሜ 6፡23

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው፡፡
የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን
በክርስቶስ ኢየሱስ ህይወት ነው፡፡ (ሮሜ 6፡23)

የኃጢአት ቅጣት እንዳለ ለልጆች ማስተማር አስፈላጊ እና በጥልቀት ሊያውቁት የሚገባ ነው፡፡ የቀረውን የወንጌል እውነት ለማወቅ መሰረት ነው፡፡ ልጆች ኢየሱስ ለምን ስለ ኃጢአቱ ሞተ? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

የሚከተሉትን ነጥቦች አስተምር

ጠይቅ፡ ደመወዝ ምንድን ነው
ደመወዝ ለሰራነው ስራ የሚከፈል ነው፡፡ እኛ በኃጢአታችን የመጣ ደመወዝ አለን፡፡ ይህም በምንሞትበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ይለየናል፡፡

ጠይቅ፡ መንግስተ ሰማይ መግባትህን በእርግጠኝነት ማወቅህ በህይወትህ ውስጥ ምን አይነት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል

መንግስተ ሰማይ መግባትህን እርግጠኛ ከሆንክ ስለ ሲኦል እና ከእግዚአብሔር ጋር ስለ መለያየት አትጨነቅም፡፡ ተስፋ፣ በራስ መተማመን እና እግዚአብሔርን የማስደሰት ፍላጐት ይጨምራል፡፡ ይህም የመኖርን አላማ ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር እንደሚወድህ ስታውቅ ሰላም እና ደስታ ይሰማሃል) (ዮሐ 5፡24፣ ዮሐ 17፡3 እና ዮሐ 10፡10)

ጠይቅ፡ እንዴት ወደ መንግስተ ሰማይ ትገባለህ?

ኃጢአታችሁ ይቅር እንዲባል እና ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝና ጌታ በመቀበል፡፡

መንግስት ሰማይ በጣም ደስ የሚያሰኝ ቦታ ነው፡፡ ኢየሱስ ሉቃ 23፡43 ላይ ገነት ብሎ ይጠራዋል፡፡ እኛም የምስራቹን ቃል ለሌሎቹ መናገር ይኖርብናል፡፡

መሸምደድ፡ የመንግስተ ሰማይ የትምህርት ክፍል

የመንግስተ ሰማይ የትምህርት ክፍልን ልጆች በእጅ ከሚሰራው ድርጊት ጋር እንዲለማመዱ አድርግ፡፡

መልካም ዜና አለኝ !

መንግስተ ሰማያት ነፃ ስጦታ ነው፡፡
የምትሰራበት ወይም ስለተገባን የምናገኘው አይደለም፡፡
‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው የእግዚአብሔር
የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ህይወት ነው››
(ሮሜ 6፡23) ‹‹ፀጋው በእምነት አድናችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
እንጂ ከእናንተ አይደለም
ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም፡፡››
(ኤፌሶን 2፡8-9)
(የጓደኛ ስጦታ ታሪክ፡ የምወደው ጓደኛዬ...)
ይህንን ስጦታ እንዳናገኝ የሚያግደን ነገር ምንድን ነው)

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፍ ገጽ 8፣ 9፣ 10 እና 11 ያለውን ተግባራት አከናውን፡፡
- በጋራ መጸለይ
- ልጆች የመንግስተ ሰማይ የትምህርት ክፍልን እና የጓደኛ ስጦታ የሚለውን ታሪክ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

የቤት ስራ

ልጆች የመንግስተ ሰማይ የትምህርት ክፍልን ጓደኛ ስጦታ ታሪክ ጋር እንዲለማመዱት ማድረግ፡፡ ቀድመው የቤት ስራቸውን የጨረሱ ልጆች የወንጌል ጐዳና ትምህርታቸውን ማጥናትና መቀጠል ይችላሉ፡፡

- የስጦታ ሳጥን ወይም የመጠቅለያ ወረቀት (የተግባር መጽሐፉ የቤት ስራ ገፆች ላይ ይገኛል፡፡)
- ሌላ የስጦታ ሳጥን ምርጫ

የስጦታ ሳጥን በትንሽ ነገር እንደ የሶፍት ካርቶን ወይም በሌላ ካርቶን በመስራት በመንግስተ ሰማይ ላይ የሚገኙ ነገሮችን በስጦታ መጠቅለያ ወረቀቱ ላይ በመፃፍ ማሳመር፡፡

የመምህሩ ማስታወሻ፡ መስታወት ውስጡ ያለው የስጦታ ሳጥን

ልጆች ስራቸውን በሚሰሩበት ወቅት መምህሩ እየተዘዋረ የልጆቹን የስጦታ ሳጥን እ የከፈተ ያሳያል፡፡ በውስጡ በታችኛው በኩል መስታወት ያለበትን ስጦታ እያስከፈተ ልጆቹን ኢየሱስ መንግስተ ሰማይ ላይ ማየት የሚፈልገው ምን ይመስልሃል) (በመስተዋቱ በሚመለከቱበት ጊዜ የሚያዩት የራሳቸውን ምስል ይሆናል)፡፡ ይህ የስጦታ ሳጥን እግዚአብሔር በኢየሱስ ለሚያምኑ የዘላለም ህይወትን እንደሰጣቸው ለማስታወስ ነው፡፡ ልጆች የስጦታ ሳጥናቸውን ለጓደኞቻቸው በማሳየት የዘላለም ህይወት ነፃ ስጦታ መሆኑን ለማብራራት እንዲጠቀሙበት ማበረታታት፡፡

ፀሎት

የሰማይ አባታችን ሆይ የዘለአለም ህይወትን በነፃ ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን፡፡ መንግስተ ሰማያት የሚያምር ቦታ ስላደረክልን ተመስገን፡፡ አሜን!



ምዕራፍ 7፡ ኃጢአት



የትምህርቱ ግቦች

- ልጆች ኃጢአትን መተርጎም/ መፍታት ይችላሉ
- ልጆች ሁሉም ሰው አንድም ሳይቀር ኃጢአተኛ መሆኑን ይረዳሉ፡፡
- ልጆች የኃጢአት የትምህርት ክፍልን ከነእጅ ምልክቱ ማለት ይችላሉ፡፡
- ልጆች የበሰበሰ ምግብ የሚለውን ታሪክ ማካፈል ይችላሉ፡፡

እንኳን ደህና መጡ፣ ጽሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

ሽርጥ፣ የማብሰያ ሳህን እና ማንኪያ በመጠቀም ማብሰል፣ ልጆች ሰላምታ መስጠት

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በመከለስ ልጆች የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንዴት እንደተጠቀሙበት መጠየቅ፡፡

የማስተማሪያ ነጥቦች

ማብራሪያ፡ የርዝመት ዝላይ

ክፍል ውስጥ ወይም በውጪ ልክ የርዝመት ዝላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጨዋታን እንዳዘጋጀው በማዘጋጀት ልጆች የተዘጋጀውን የማይደረስበት መስመር ላይ እንዲዘሉ ማድረግ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ የደረሰበትን መመዝገብ በድንጋይ ወይም በእንጨት ነገር መመዝገብ፡፡

ውይይት፡ የርዝመት ዝላይ

ስታስበው ተለቅ ያለ የሩጫ መጀመሪያ ብትደርግ ኖር ምልክቱ ላይ ዘለህ የምትደርስ ይመስል ሃል? የተሻለ ተለማምደህስ ቢሆን ኖሮ?ለውጥ የሚያመጣ ይመስልሃልአይደለም፡ ግቡ ሊደረስ በት የሚችል አይደለም

ውይይት፡ ኃጢአት

<u>መጠየቅ፡ እግዚአብሔር እንድንከታተለው ያሰቀመጠው መሰፈርት ምን ዓይነት ነው?</u>

በማቴ 5፡48 መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንግዲህ በሰማይ ያለው አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ፍጹ ማን ሁኑ፡፡ምንም ያህል ብንጥር ፍጹም ልንሆን አንችልም አይደል) በእግዚአብሔር መለኪያ እኛ ልንለካ አንችልም እግዚአብሔር ፍፁም ነው፡፡ እኛ ፍፁም ልንሆን ስለማንችል መለኪያው ን መጠቀም አንችልም፡፡ ለምንድን ነው ፍፁማን መሆን አንችልም) ምክንያቱም ኃጢአት ነው፡ ፡ ሁላችንም ኃጢአት ነው ሁላችንም ኃጢአተኞ ነን፡፡

ጠይቅ፡ ኃጢአት ምንድን ነው?

ኃጢአት እግዚአብሔርን እና ቃሉን ያለመቀበል ውጤት ነው፡፡ ኃጢአት ማለት እንደ መዋሸት፣ መስረቅ፣ ማታለል ወላጆቻችንን አለመታዘዝ ያሉ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን የማያስደሰት የምናስበው፣ የምንለው፣ የምናደርገው ወይም የማናደርገው ሁሉ ነው፡፡ መዋሸት፣ መስረቅ፣ መግደል እና መጥፎ ነገሮችን ማሰብ ኃጢአቶች እንደሆኑ እናውቃለን፡፡ ግን ማድረግ የሚገባንን አለማድረግ ኃጢአት መሆኑን ይነግረናል፡፡ ሁሌም እግዚአብሔርን አለመውደድ፣ እግዚአብሔርን አለማመን፣ የተቸገሩ ሰዎችን አለመርዳት፣ መጽሐፍ ቅዱስ አለማንበብ አለመጸለይ ሁሉ ኃጢአቶች ናቸው፡፡

በአማራጭነት፡

ጠይቅ፡ ኃጢአት ከየት መጣ?

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሮሜ 5፡18-19 ሲናገር... እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት (አዳም) ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደመጣ እንዲሁም የአንድ ጽድቅ (ክርስቶስ) ምክንያት ስጦታው ህይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ፡፡ አንድ ሰው (አዳም) ኃጢአትን ወደ ሰው ልጆች አመጣ አንድ አምላክ-ሰው (ኢየሱስ ክርስቶስ) ፀጋን አመጣ፡፡

አዳምና ሔዋን ኃጢአት ሲሰሩ ለኃጢአታቸው የሚከፍል አዳኝ እንደሚመጣላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር፡፡ ፍፁፍ የሆነ መስዋዕት ከመምጣቱ በፊት የአንሰሳ ደም በማፍሰስ ለኃጢአት ስርየት ይደረግ ነበር፡፡ የእንስሳቱ ደም/መስዋዕትነት ይደረግ የነበረው የሚመጣውን ለማመልከት ነበር፡፡ ይህም አዳኙ ኢየሱስ በፍፁምነት በመኖር እና ለኃጢአታችን ዕዳውን የሚከፍል ነበር ፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝሙር ሮሜ 3፡23 እና ማቴ 5፡48 መዝሙሮች

ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል ይህ ሃቅ እና
የሰው ልጅ የሚያደርገው ነው፡፡
እኛ በራሳችን ፍጹም መሆን አንችልም፡፡
እግዚአብሔር ደግሞ መንግስተ ሰማይ
ሊያስገባን ይፈልጋል
ለዚህም መንገዱ ኢየሱስ ነው፡፡

ድራማ፡ የኃጢአት ባርነት

(ለዚህ ጭውወት/ ቀልድ ጥቁር ልብስ መጠቀም ልጆችን ለዚህ ማብራሪያ አትጠቀም))

አዋቂ መሪ በክፍሉ መሃል ላይ ጥቁር ልብስ ለብሶ እንዲቆም በማድረግ አይኑንና ጆሮውን በመሸፈን እጅና እግሩን መንቀሳቀስ እንዳይችል አድርጐ ማሰር፡፡ መሪዎች ይህንን ድራማ በሚሠሩበት ወቅት የሚቀጥለውን አጥኑት፡

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይለየናል፤ ጨለማ ውስጥ ያስገባናል፣ ጠፍሮ በመያዝ ባሪያዎች ያደርገናል፡፡ በራሳችን ከኃጢአት ልንላቀቅ አንችልም፡፡ ከሰይጣን ጋር በመጣበቅ ለእግዚአብሔር መልስ እንዳንሰጥ ያደርገናል፡፡ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡19 ሲናገር ‹‹... ሰው ለተሸነፈለት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና፡፡››

አንድ ሰው መጥቶ የተጠመጠመውን የኃጢአት ወጥመድ ይፈታዋል፡፡ ይህ ሰው በእርግጠኝነት ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ንስሃ በመግባት እና ከኃጢአታችን በመመለስ ከኃጢአት ነፃ ልንወጣ እንችላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃ ሁሉ ሊያነፃን የታመነ እና ፃድቅ ነው፡፡›› (1ዮሐ 1፡9)

ታሪክ፡ የተበላሸ ምግብ ታሪክ

ጥሩ ሰው በመሆን መንግስተ ሰማይ በመግባት መሞከር በተበላሸ የምግብ ቁሳቁስ ማብሰል ማለት ነው፡፡ ሁሉም የምግብ ቁሳቁሶች ንፁህ ቢሆኑ እንኳን የተበላሸው ነገር ምግቡን በሙሉ ያበላሸዋል፡፡ በእግዚአብሔር አይን ኃጢአታችን (መጥፎ አስተሳሰባችን ወይም ፀያፍ ቃሎቻችን የሰራነውን ጥሩ ነገር ሁሉ ያበላሹታል፡፡ ጥሩ እና ትክክል መሆን ወይም ትንሽ የተበላሸ ነገር የእግዚአብሔርን የፍፁምነት መለኪያ ሊያሟላ አይችልም፡፡ ታዲያ እንዴት ራሳችንን ማዳን እንደማንችል አያችሁ)

ታሪኩን ከነገርክ በኋላ ልጆች ታሪኩን መናገር እንዲለማመዱ አድርግ፡፡

(ይህን ታሪክ ልጆች በደንብ በማያውቃቸው እና ባህላዊ በሆኑ ምግቦች ማሳየት ውጤታማ ነው፡ ፡ ለምሳሌ ውሃ ውስጥ መርዝ ገብቶ በሚል ማሳየት ይቻላል፡፡)

ማብራሪያ፡ በቀን ሶስት ኃጢአት

ሰዎች በቀን ስንት ጊዜ ኃጢአት የሚሰሩ ይመስላችኋል) እስቲ በቀን ሶስት ጊዜ እንበል አንዴ ባይታዘዝ፣ አንዴ ንዴቱን መቆጣጠር ቢያቅተውና አንዴ መጥፎ ነገር ቢያስብ እንበል፡፡ ይህ ማለት በቀን ሶስት ኃጢአት በአመት በ1000 በላይ ይመጣል፡፡

70 አመት ትኖራለህ ብንል በህይወት ዘመን 70000 ኃጢአት ይሰራል ማለት ነው፡፡

እንደዚህ ብዙ ወንጀል ብትሰራ እና ወደ ዳኛ ብትሄድ ምን የሚፈረድብህ ይመስልሃል?

አንድ ኃጢአት ፍፁምነትን ሊያበላሽ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ሲናገር የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ፍጹማን ሁኑ (ማቴ 5፡48) እንዴት ራሳችንን ማዳን እንደማንችል አያችሁ?

መሸምደድ፡ ኃጢአት የሚለውን የትምህርት ክፍል

ኃጢአት የሚለውን የትምህርት ክፍል ልጆች ከእጅ ማሳያው ጋር እንዲለማመዱት አድርግ፡፡

ይህንን ስጠኝ እንዳናገኝ ምን አገደን?

ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን እራሳችን ማዳን አንችልም፡፡
ኃጢአት ምንድነው?የምንናገረው፣ የምሰራው ወይም
የማንሰራው እግዚአብሔርን ሊያስደስት የማይችል ነገር ነው፡፡
‹‹ሁሉም ኃጢአት ሠርተዋል፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል››
(ሮሜ 3፡23)

(በአማራጭነት)
‹‹የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍፁማን ሁኑ›› (ማቴ 5፡48)
(የተበላሸው ምግብ ታሪክ፡
ጥሩ በመሆን መንግስተ ሰማይ ለመግባት መሞከር ...)

የተለየ መንገድ መኖር አለበት- የእግዚአብሔር መንገድ

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፍ ገጽ 12 13 እና 14 ላይ የሚገኙትን ተግባራት አከናውን፡፡
- ኃጢአት የሚለውን የትምህርት ክፍል ከተበላሽ ምግብ ታሪክ ጋር በማያያዝ ልጆች እንዲለማመዱት አድርግ፡፡
- በጋራ መጸለይ፡፡

- **የኃጢአት ወረቀት (በአማራጭነት)**
  ልጆች አንድ ወረቀት ወስደው ሁለት ቦታ እንዲያጥፉት በማድረግ በውስጠኛው ገጽ ላይ የሚያስቸግራቸውን ኃጢአት ይፃፉ፡፡ ኃጢአትቸውን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው በመጠየቅ እና ይቅር ስላላቸው እንዲያመሰግኑ ጊዜ መስጠት፡፡ በመቀጠል ኃጢአታቸውን የፃፉበትን ወረቀት ቀዳደው እንዲጥሉ ማድረግ ይቅር እንደተባሉ ማመን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹ኃጢያታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነ እና ፃድቅ ነው›› (ዮሐ 1፡9)

የቤት ስራ

- **የኃጢአት ሰንሰለት**
  ልጆች በትንሽ ወረቀት ላይ ኃጢአታቸውን እንዲጽፉ በማድረግ ከወረቀት ሰንሰለቱ ጋር በማጣበቅ በአንደኛው በኩል በሮሜ 6፡23ሀ በኩል ‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው›› የሚለውን በሁለተኛው በኩል ደግሞ በሮሜ 6፡23ለ ‹‹የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ህይወት ነው›› የሚለውን ማጣበቅ፡፡

ስራውን ቀድመው የጨረሱ ልጆች የወንጌል ጐዳና ትምህርታቸውን መለማመድ/ ማጥናት ይችላሉ፡፡ ስለ ይቅርታ አዎንታዊ ነገሮችን በመናገር እና (1ዮሐ 1፡9) በማስታወስ ኢየሱስ አምላክ ነው ከሰማይ የመጣውም ስለ እኛ ሲል በመስቀል ለመሞት ነው የሚለውን ጥቅስ በከፍተኛ ድምፅ ማስጠናት፡፡

ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ ለእኛ ስላለህ ፍቅር እናመሰግንሀለን፡፡ ኃጢአተኞች ሳለን ልጅህን ኢየሱሰን ይቅር ስላልከን እናመሰግንሃለን፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፀለይን አሜን



የትምህርት ግቦች

- ልጆች እግዚአብሔር ቅዱስ፣ አፍቃሪ እና ትክክል መሆኑን ይረዳሉ።።
- ልጆች እግዚአብሔር የሚለውን የትምህርት ክፍል ከነእጅ ማሳያው ማለት ይችላሉ።።

እንኳን ደህና መጡ፣ ጸሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

የቡድን መሪው ትልቅ አበባ ከነትልቅ ቅጠሉ ይይዛል።።

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በመከለስ ልጆች የቤት ስራቸውን እንዴት የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት እንዲያብራሩ አድርግ።።

የማስተማሪያ ነጥቦች

ውይይት፡ እግዚአብሔር

ልጆች ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የእግዚአብሔርን ባህርያት በማንበብ በተግባር መጽሐፍ ገጽ 16 መሠረት በአበባው ቅጠሎች ላይ ይጽፋሉ።።

የእግዚአብሔር ፈጣሪነት
‹‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን ምድርን ፈጠረ›› (ዘፍ 1፡1)

ልጆች እግዚአብሔርን እንዲገልፁት አድርግ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጹም በስራውም ትክክል እንደሆነ ይነግርናል (ዘዳ 32፡4)
እግዚአብሔር ቅዱስ ነው (ዕምባቆም 1፡13፣ ኢሳ 6፡3)
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም (ኢሳ 40፡25)
እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፡8)
እግዚአብሔር ትክክል ነው (ዘጸ 34፡7ለ)
እግዚአብሔር ብርሃን ነው (1ዮሐ 1፡5)
እግዚአብሔር መንፈስ ነው (ዮሐ 4፡24)
የእግዚአብሔር ምህረት ከህይወት ይሻላል (መዝ 63፡3)

ከመዝሙር 145 እና 3 የተመረጡ ጥቅሶችን ማንበብ

እግዚአብሔር ቅዱስ አፍቃሪ እና የምህረት አምላክ ነው። ሊቀጣን አይፈልግም። ነገር ግን ትክክል ስለሆነ ኃጢአተኛውንም ይቀጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ስለ እርሱ ማወቅ ያለብንን ነገር ይነግረናል። የእግዚአብሔርን ፍጹምነት ለማወቅ እግዚአብሔር ፃድቅ መሆኑን መረዳት አለብን። እግዚአብሔር የኛን ኃጢአት ማየት አይፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹አይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንፁህን ናቸው፣ ጠማማውንም ልትመለከት ዘንድ አትችልም›› (ዕንባቆም 1፡13)

ባለፈው ሳምንት ለኃጢአታችን መንፈሳዊ ሞት ወይ ከእግዚአብሔር በመለየት እንደምንቀጣ ተምረናል። በተጨማሪም ኃጢአት መቀጣት እንዳለበት እና የኃጢአትም ቅጣት ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት መሆኑን ተምረናል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአትን ዕዳ ከፍሎልናል። በኢየሱስ በማመን ከኃጢያታችን ነፃ እንወጣለን ከእግዚአብሔር ጋር እንታረቃለን።

እግዚአብሔርን እና ባህሪዎቹን ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። በመጽሐፉ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ሶስት ስብዕና እንዳለው እንመለከታለን። በዚህ ምክንያት ነው ስላሴ የምንለው እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።

መዝሙር፡ ስላሴ

ስለ ስላሴ መዝሙር ማስተማር

- እግዚአብሔር አብ (የፍሬ ጃኮስን መዝሙር በክብ ቅርፅ ቅማችሁ አስምሩ)

እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር አብ
እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር ወልድ
እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

- ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

ድራማ ሁለት ጓንቶች

መሪው ትልቅ ነጭ ጓንት በማድረግ በቀኝ እጁ ላይ አፍቃሪ በግራ እጁ ላይ ደግሞ ትክክል በማለት ይጽፋል። ቀኝ እጁን በማንሳት በአንድ በኩል እግዚአብሔር ይወደናል ይላል። ግራ እጁን በማንሳትና በማወዛወዝ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ትክክል ነው በማለት ግራ እጁን ያወዛውላል።

የመነቃቂያ ጨዋታ ሁለት ልጆች አጠገብ ለአጠገብ ይቆማሉ አንደኛው ልጅ በአንድ እጁ አፍቃሪ የሚል ጽሁፍ የተፃፈበትን ጓንት ያደርጋል ሌላኛው ልጅ በአንድ እጁ ትክክል የሚለውን ጓንት ያደርጋል። ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን የትምህርት ክፍል ልብ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እንዳለ ሰው አብረው ይሉታል።

ታሪክ ፡ ቅጣት

የቅጣት (ቅያሪ) ታሪክ በድራማ መልክ በቡድኑ ከተሰራ በኃላ ሊነገር ይችላላ የእግዚአብ ሔርን ፍቅር እና ትክክለኛነት የምናብራራበት ታሪክ ነው፡፡

ከረጅም ጊዜ በፊት አንድ ቡድን ይመራ የነበረ መሪ ነበረ፡፡ ቡድኑ ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ድንኳን ላይ/ አካባቢ ሰፍረው ነበር፡፡ እነኚህ ቡድኖች ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ነበሩ ሲሄዱም ልጆቻቸውን የሚሄዱት፡፡ አንድ ምሽት ላይ የአንደኛው /መሪው ሁለተኛ ሰው መጥቶ ከምግብ ማከማቻ ድንኳኖች ውሰጥ አንድ ሰው ምግብ እንደ አስደናቂ ነገረ ው፡፡ መሪውም በጣም ተናደደ ምክንያቱም የነበረው የምግብ አቅርቦት አነስተኛ በመሆ ኑ ለሁሉም በስርዓት መታደል ስለነበረበት ነው፡፡ ከዛም መሪው የቡድኑን አባላት ሰብ ስቦ ከአሁን በኋላ እህል ሲሰርቅ የተገኘ ሰው በአደባባይ እንደሚገረፍ ተናገረ፡፡

ይህን ካወሩበት ምሽት ብዙም ሳይቆይ የመሪው ምከትል መጥቶ በድግሚ ተጨማሪ ምግ ብ መሠረቁና ሌባው ግን መያዙን ለመሪው ነገረው፡፡ የሰረቀችውም የመሪው እናት መሆ ናቸውን ነገረው፡፡ (አስፈላጊ ከሆነ የራሱ የመሪው እናት ብሎ መቀየር ይቻላል)፡፡ መሪው በጣም ተቸገረ፡፡ ያረጀችውን እናቱን እንድትገረፍ ቢያደርግ ልትሞት እንደምትችል ያውቃል፡፡ ካልቀጣት ደግሞ ህዝቡ እሱ ላይ ያለውን የመሪነት አመኔታ ሊያጣ ይችላል፡ ፡

ሁሉም ምን ሊያደርግ እንደሚችል በመገረም ይጠባበቁ ነበር፡፡ በመቀጠል መሪው የተደረ ገውን ስርቆትና ቅጣቱም በአደባባይ መገረፍ መሆኑን ተናገረ፡፡ በመቀጠል ሁሉንም ሰው ያስደነነገጠ ነገር አደረገ ሸሚዙን በማውለቅ ምክትሉን በእናቱ ፍንታ እንዲገርፈው አዘዘ፡ አያችሁ፣ በዚህ መንገድ ፍትህን ማስፈን በሌላ በኩል ደግሞ ለእናቱ ያለውን ፍቅር መግ ለጽ ይችላል፡፡ ቅጣቱን በመቀጣት ፍትህን አሰፈነ ነገር ግን መሪው እናቱን ስለሚወድ ለእርሷ የነበረውን ቅጣት ተቀጣላት፡፡

እኛም ልክ እንደመሪው እናት ነን፡፡ ስለሰራነው ኃጢአት መቀጣት ሲኖርብን እግዚአብ ሐር ግን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ሙሉ ቅጣታችን ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን እንዲከፍል አደረገው፡፡

ማብራሪያ፡ የባንክ ዘራፊው በአማራጭ

ይህ ማብራሪያ እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ ያሳያል፡፡

ከባንክ ቤት ዘርፌ ስወጣ ስውር ካሜራ ቀረፀኝና ተይዤ ዳኛ ፊት ቀረብኩ እንበል፡፡ ዳኛው ‹‹ምን ብለህ ነው የምትከራከረው)›› ሲለኝ ‹‹ጥፋተኛ ነው የምለው ክቡር ፍርድ ቤት›› ነው ብዬ የምመልሰው ምክንያቱም ማስረጃዎቹ ሁሉ በግልጽ ይህን ስለሚያሳዩ፡፡ ‹‹ነገር ግን በጥፋቴ ተፀጽቻለሁ የወሰድኩትንም ገንዘብ እመልሳለሁ በነፃ ከተለቀኩ ዳግ መኛ እንዲህ አይነት ነገር ላለማድረግ ቃል እገባለሁ፡፡›› ስል ዳኛው ሰምቶ የሚለቀኝ ይመስላችኋል) ፍትሃዊ ይሆናል) አይሆንም ለእያንዳንዱ ወንጀል ምን መቀጣት እንዳለ በት የሚያስቀምጥ መስፈርት አለ፡፡፡ እግዚአብሔርም ጋር እንደዚህ ነው፡፡ የኛን ኃጢ አት የሚቀጣበት የራሱ የሆነ መስፈርት አለው፡፡

መሸምደድ፡ እግዚአብሔር የሚለውን የትምህርት ክፍል

የተለየ መንገድ መኖር አለበት የእግዚአብሔር መንገድ

እግዚአብሔር ፃድቅ የፍቅር አምላክ እና ትክክል ነው በአንድ በኩል እግዚአብሔር ይወደናል ሊቀጣን አይፈልግም በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ትክክል እና ፍትሐዊ ስለሆነ ኃጢአታችንን መቅጣት አለበት፡፡

እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፡8)

(በምርጫ)
‹‹ኃጥያተኛውን ሳይቀጣ አያልፍም››
(ዘፀአት 34፡7)

(የቅጣቱ ታሪክ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት ይህንን ችግር ፈቶታል)

ችግሩ ይታይሀል?
እግዚአብሔር ልጁን በመላክ ይህንን ችግር ፈቶታል፡፡

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፍ ገጽ 15፣ 16 እ ና 17 ያለውን አከናውን፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር የሚለውን የትምህርት ክፍል እና ቅጣት የሚለውን ጨዋታ እንዲለማመዱ ማድረግ
- በጋራ መጸለይ

የቤት ስራ

የቤት ስራቸውን ቀደም ብለው የጨረሱ ልጆች የወንጌል መንገድን መለማመድ ይችላሉ፡፡

- በእጃችሁ መጻፍ ላይ በአንደኛው አፍቃሪ በሌላኛው ትክክል ብላችሁ ፃፉ፡፡
- ስለ ስላሴ የተሰጠውን የእጅ ስራ የፒራሚድ ቅርጽ ያለው ወረቀት በመስራት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ በ1ኛው እግዚአብሔር አብ በሁለተኛው እግዚአብሔር ወልድ በሶስተኛው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብላችሁ ፃፉበት፡፡

ፀሎት

የሰማዩ አባታችን ሆይ ስለወደድከን እናመሰግንሃለን የበለጠ እንድናውቅህ እና እንድን ወድህ እርዳን፡፡ አሜን!



ምዕራፍ 9 ክርስቶስ



የትምህርቱ ግቦች

- ልጆች ክርስቶስ ማን እንደሆነ እና ምን እንዳደረገ ይረዳሉ
- ልጆች ክርስቶስ የሚለውን የትምህርት ክፍል ከነእጅ ማሳያው መድገም ይችላሉ።።
- ልጆች ወንጌልን የመናገር ብቃት እና ፈቃደኝነት ይኖራቸዋል።።

እንኳን ደህና መጡ፣ ጸሎት፣ ምስጋና እና መዝሙር

የቡድን መሪዎች ዘውድ ያደርጋሉ።።

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ እና የምዕራፍ 4 የምስራቹ ቃል ትምህርትን በመከለስ ልጆች እን ዴት የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለማካፈል እንንደተጠቀሙበት ጠይቅ።።

የማስተማሪያ ነጥቦች

መጽሐፍ ቅዱስ፡ የዮሐንስ ወንጌል

የዮሐንስ ወንጌል (ዮሐ 1፡1-14) ኢየሱስን ቃል ሲል ይገልጸዋል።። ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር።። ቃልም በእግዚአብሔር ነበር ቃልም እግዚ አብሔር ነበር ቃልም ስጋ ሆነ ፀጋንና እውነትም ለብሶ በእኛ አደረ አንድ ልጅም ከአ ባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብር አየን።።››

ውይይት፡ አምላክ ሰው ነው (በአማራጭነት)

ኢየሱስ አምላክም ሰውም ነው ማለት ምን ማለት ነው አዲስ ቃል እንማር እንደ ሰው ስጋ መልበስ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹ኢየሱስ ስጋ የለበሰ አምላክ ነው›› ይላል።። ይህ ማለት በስጋ የተገለጠ በስጋ ውስጥ አደረ ማለት ነው።። ኢየሱስ ተራ ሰው አይደለም።። ኢየሱስ አምላክም ሰውም ነው ሰማይን ትቶ ሲመጣ እንደኛው ስጋና ደም ነበር።። ኢየ ሱስ አምላክ ነኝ ያለ ብቸኛው ሰው ሲሆን ይህንንም የሚያረጋግጥ ተአምራቶችንም ሰር ቷል ።። ከሁሉም የሚበልጠው ተአምር ደግሞ ከሞት መነሳቱ ነው።። ይኼ ደግሞ ክርስ ትናን ከሌሎች ኃይማኖቶች ልዩ ያደርገዋል።።

ድራማ፡ የመሰላሉ ቀልድ /ሞኩውውት

አንደ ወንድ መሪ በመሰላሉ ጫፍ ላይ ዘውድ በማድረግ ጋዎን በመልበስ በአንድ ፊ ቱ አምላክ በሌላ በኩል ሰው የሚል ጽሑፍ ያለው ምልክት በአንገቱ ላይ እንዲያደርግ ማድረግ፡፡

አንድ ሰው ዮሐንስ 1፡1 እና 14 ያንብብ.

በአንድነት ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡ ከሰማይ ወደ ምድር መጣ ሲባል መሪው ዘውዱንና ጋወኑን በማውለቅ ከደረጃው ወደ ታች ይወርዳል፡

ኢየሱስ ክብሩን እና መንግስተ ሰማያትን በመተው ሰው ለመሆን መጣ ነገር ግን አም ላክነቱን ለማጣት ወይም በመተው አይደለም (ዮሐ 1፡29) በብሉይ ኪዳን ጊዜ አይሁዳ ውያን ለኃጢአት ስርየት ያቀርቡት የነበረው በዛ ነበር፡፡ እንደ መስዋዓትነት ለመቅረ ብ በጉ ንፁህና ጤነኛ መሆን አለበት፡፡ ኢየሱስም ይህን ንፁህ በግ በመተካት በምድር ላይ ፍጹም ህይወት ኖሮ ለኃጢአታችን የሚከፈል መስዋዕት ሆነልን፡፡

ሞኩውውቱን ለማዳበር ፊሊ 2፡5-11 መጠቀም

<u>ውይይት፣ ኢየሱስ አምላክ ነው (በምርጫ)</u>

<u>ውይይት፡ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ እንዴት አረጋገጠ?</u>

በታሪክ ውስጥ አምላክ መሆኑኑ በስራው ያሳየው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ አምላ ክ ነው፡፡ በሽተኛውን ደካማውን አይነ ስውሩን ፈውሷል፡፡ ባህርና ንፋሱን መቆጣጠር ችሏል፡፡ በብዙ ጊዜ የሞቱ ሰዎችን አስነስቷል፡፡

<u>*ጠይቅ፡ የጽድቅ ህይወት መኖሩ ለምን ሰማይ አስፈላጊ ሆነ?*</u>

አንድ ሰው ብቻ የእግዚአብሔርን የፍጹምነት መስፈርት ያሟላ ኑሮ መኖር ችሏል፡፡ ኢየሱስ እኛ ልንኖረው ለማንችለውን ፍጹም ህይወት በመኖር ለኃጢአታችን ክፍያ የሚሆነውን የእግዚአብሔር መስፈርት አሟላ፡፡

<u>*ጠይቅ፡ ኢየሱስ ለምን ሞተ?*</u>

በኃጢአት እዳ ተይዘህ ስለነበር የማስለቀቂያ ቤዛ ስለ እኛ መከፈል አለበት፡፡ ይህም ዋጋ ኃጢአት የሌለበት የፃድቅ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነበር፡፡ የኃጢአታችን እዳ በመስቀል ላይ በመሞት ከፈለ፡፡

የተጠቀመውን የበግ ምስል ማሳየት መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር በግ ይለ ዋል፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ሲናገር እነሆ የአለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ (ዮሐ 1፡29) በብሉይ ኪዳን ጊዜ አይሁዳውን ለኃጢአት ስርየት ያቀርቡት የነበረው ቤዛ ነበር፡፡ እንደ መስዋዕትነት ለመቅረብ በጉ ንፁህና ጤነኛ መሆን አለበት፡ ፡ ኢየሱም ይህን ንፁህ በግ በመተካት በምድር ላይ ፍፁም ህይወት ኖሮ ለኃጢአታችን የሚከፈል መስዋዕት ሆነ፡፡

እግዚአብሔር የኃጢአታችን ዋጋ የበደላችንን ቅጣት እንዲከፍል ላከው። ኢየሱስ በመስቀል ሲሞት ተፈጸመ ያለው የኃጢአታችን እዳ ሙሉ በሙሉ ተከፈለ ማለት ነው።

ታሪክ፡ መጽሐፈ ኃጢአት

ማስታወሻ ለዚህ ማብራሪያ በምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱስ አትጠቀም። ማብራሪያው መጽሐፍ የሚያስፈልገው ስለሆነ ሌላ መጽሐፍ መጠቀም። ነገር ግን ምንም አይነት መጽሐፍ ማግኘት የማይቻል ከሆነ ወረቀት ወይም ትልቅ ቅጠል መጠቀም ይቻላል።

በግራ እጅህ መጽሐፉን ከፍ አድርገህ በመያዝ ይህ እጄ እኔን ይወክላል እንበል፣ ይህ መጽሐፍ ደግሞ የሰራሁትን ኃጢአት ያሳያል በማለት መጽሐፉን ከፍ አድርገህ አሳይ አስፈላጊ ከሆነ የኃጢአትን ትርጉም አስታውሰህ ተናገር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በመስራቴ የማልደሰትባቸው ነገሮች አሉ። ችግሩ ያለው እዚህ ጋር ነው ፡ የኔ ኃጢአት ነው።

በቀኝ እጅህ ግራህን በመያዝ ይህ እጄ እግዚአብሔርን ይወክላል እንበል። ይዘህ እጅህ በቀኝ እጅህን ከታች በኩል በመደገፍ እግዚአብሔር ይወደኛል ትላለህ ከዚያም መጽሐፉን በመጠቆም ነገር ግን እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል። ቀኝ እጅህን በማንሳት ኃጢአትን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ እንዳልችል አደረገኝ ብለህ ተናገር።

ቀኝ እጅህን ከግራህ እኩል በማሳየት እግዚአብሔር ይህንን ችግሬን ኢየሱስን ከሰማይ ወደ ምድር በመላክ ፈቶታል በማለት ተናገር። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በእርሱ ኢየሱስ ላይ አኖረ ኢሳ 53፡6 መጽሐፉን ከቀኝ ወደ ግራ እጁ በማዛወር ፍጹም ህይወት ኖሮ ስለ ኃጢአቴ በመስቀል ላይ ሞተ ተቀበረ ብለህ ተናገር። ፡ መጽሐፉን ከጠረጴዛ ስር በማስቀመጥ በሶስተኛውም ቀን ከኃጢአት ተነሳ በማለት ቀኝ እጅህን ወደ ላይ ከፍ አድርገህ አሳይ።

ኃጢአቴ ከተሰረየልኝ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ እችላለሁ በማለት ሁለት እጆችህን ማጨብጨብ። ከዚያም በላይ እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ መንግስተ ሰማያት የዘላለም ህይወት ስጦታን ሰጥቶናል።

መሸምደድ፡ ክርስትስ የሚለውን የትምህርት ክፍል

ችግሩን ማየት ትችላለህ?
ኢየሱስን በመላክ እግዚአብሔር ይህን ችግር ፈቶታል።

ኢየሱስ አምላክ ነው።
ከሰማይ ወደ ምድር መጣ
ፍጹም ህይወት በምድር ላይ ኖረ
ስለ ኃጢአታችን እዳ ለመክፈል በመስቀል ሞተ።
ከሞት በመነሳት አሁን በመንግስተ ሰማይ ሆኖ ለእኛ የዘላለም
ህይወት ግብጣ ያቀርባል።

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እንዳይጠፋ እስኪሰጥ ድረስ አለምን
እንዲሁ ወዷልና”
(ዮሐ 3፡16 አመት)
(የኃጢአት መጽሐፍ ታሪክ፡ ይህ እጅ የሚወክለው...)
ይህን ስጦታ እንዴት ማግኘት እንችላለን? በእምነት

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፉ ገጽ 18 19 እና 20 ላይ ያሉትን ተግባራት አከናውን።።
- ክርስቶስ የሚለውን ትምህርት እንዲለማመዱ እና የኃጢአት መጽሐፍ የሚለው ን ታሪክ እንዲያጠኑ።።
- በጋራ መጸለይ.

የቤት ስራ

የቤት ስራ የተግበር የቤት ስራቸውን የጨረሱ ልጆች የወንጌልን ጦዳና ጥናታቸውን መ ቀጠል ይችላሉ።።.

- ዘውድ
- መስቀል በአማራጭነት ልጆች ከእንጨትና ከገመድ መስቀል ይሰራሉ።።.

ይህ ዘውድ ኢየሱስ ለኃጢአትችን ዋጋ ለመክፈል ከሰማይ ቤቱን ትቶ መምጣቱን ያስ ታውሰናል።። አሁን ኢየሱስ በመንግስተ ሰማያት ስለ እኛ እየማለደ ኃጢአት ስንሰራ እ ግዚአብሔር ይቅር እንዲለን እየጠየቀ ይገኛል።። ምክንያቱም እርሱ ስለእኛ ቅጣታችን ን ተቀጥቷልና።። በሚመጣውም ሳምንት ይህንን ለሌሎቹ ሰዎች አካፍሉ።።.

ፀሎት

ጌታ ኢየሱሱ ሆይ ስለ እኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ ስለሞትክ እና የዘላለም ህይወት ል ትሰጠን ስለወደድከን እናመሰግንሃለን አሜን.





የትምህርቱ ግቦች

ልጆች የእውቀትን ጊዜያዊ እምነትን እና የሚያድነውን እምነት ልዩነት ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

- ልጆች የእምነት የትምህርት ክፍልን ከነእጅ ማሳያው መድገም ይችላሉ፡፡
- ልጆች ከሆነውና ካልሆነው በመጀመር የአዳኝ እምነትን ትርጓሜ ማወቅ ይችላሉ፡፡ .

እንኳን ደህና መጡ ጸሎት,ምስጋና,መዝሙር

የቡድን መሪዎች ለልጆች ፊኛዎችን በመንፋት ሰላምታ ያቀርባሉ

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በመከለስ ልጆቹ እንዴት የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙት ጠይቅ፡፡.

የማስተማሪያ ነጥቦች

ውይይት፡ አዳኝ እምነት ያልሆነው

- <u>እውቀት</u>

  የመዳን እምነት ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ልክ---------- የአንድ ታዋቂ ሰው ምስል ማሳየት እንደሚያምኑበት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደዚያው ሊያምኑት ይፈልጋል፡፡ ይህ ሰው በእውነት በህይወት እ ንዳለ ታውቃለህ ለአንተ አሁን የሆነ ነገር ሊያደርግልህ እንደሚችል ትተማመ ናለህ ስለዚህ ስለ አንድ ሰው ማወቅ ብቻውን የሚያድን እምነት ሊሆን አይችል ም፡፡

  ሌላ ማን እግዚአብሔር እንዳለ ያምናል) ማን እውቀት አለው) መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ሰይጣንም እግዚአብሔር እንዳለ ይምናል ይላል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ አጋንንትም ደግሞ ያምናሉ ይን ቀጠቀሱማል›› (ያዕ 2፡19) ስለዚህ እግዚአብሔር በመኖሩ ማመን ብቻ የሚያድ ን እምነት ሊሆን አይችልም፡፡

- <u>ጊዜያዊ እምነት (‹‹ለአሁን ብቻ››)</u>

ልክ ችግር ሲገጥመን ወደ እግዚአብሔር እንደምንጮኸው ወይም የሆነ ነገር ስንፈልግ ልክ ፈተና ሲደርስ እርዳታ እንምንፈልግ ከክፉ የሚጠብቀን ስንፈልግ ወይ ሲያመን እንደምናምነው የወደደን እምነት እንደዚያ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር እንዲረዳን ጠየ ቅ ችግር የለውም ግን የመዳንን እምነት አይወክልም፡፡

ማብራሪያ፡ ፊኛዎችን በመንፋት (አረፋዎችን መንፋት)

አረፋዎቹን በመስራት ጊዘአዊ ለአሁን ብቻ እምነትን ለማብራራት ተጠቀም፡፡ አረፋዎቹ እንዴት በቀላሉ እንደሚጠፉ አሳይ

መጠየቅ፡ ለአሁን ብቻ የሆነ እምነት ምሳሌ ማን ሊሰጠን ይቻላል?

ውይይት፡ የመዳን እምነት ምንነት

የመዳን እምነት - የመዳን እምነት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የዘለአለም ህይወት እን ደሚሰጥ እንደግል አዳኝ ማመን ማለት ነው፡፡

ማብራሪያ፡ ቁልፎች በአማራጭነት

በአንድ ላይ የተሰሩ ቁልፎችን አመልክት፡፡ በመቀጠል ቁልፎቹ እንዴት እንደሚመሳ ሰሉ አሳይ፡ ነገር ግን የቤትህን ቁልፍ ሊከፍት የሚችለው አንደኛው ብቻ ነው፡፡ ልክ እነዚህ ቁልፎች እንደሚመሳሰሉት ሁሉ ብዙ አይነት እምነቶችም አሉ፡፡ ነገር ግንየመንግስተ ሰማያትን በር የሚከፍተው ቁልፍ አንድ ብቻ ነው ይህም የመዳን እም ነት በመባል ይታወቃል፡፡

ድራማ፡ የጀልባው ታሪክ

ታሪኩን ከተናገርክ በኋላ ልጆቹ በድራማ መልክ እንዲሰሩት አድርግ፡፡ ለድራማው ሁለት ፈቃደኛ ተማሪዎች የጀልባው ካፒቴንና አሳ አጥማጅ እንጨት ጣውላ ነፍ ስ አድን በገመድ የታሰረ ያስፈልጋል፡፡

በጀልባዬ ውስጥ ከመሬት ርቄ ብቻዬን እየተጓዝኩ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ሁሉ ነገር ጥሩ ነበር ነገር ግን ትንሽ እንደቆየሁ በጀልባዬ ላይ ውሃ የሚያስገቡ ቀዳዳዎች አስተዋልኩ፡፡ ቀዳዳዎቹን ለመድፈን ከፍተኛ ሙከራ አደረኩ ነገር ግን ጀልባዬ ከመስጠም አላዳነኝም በመጨረሻ አንድ እንጨት ይዤ ከመስጠም ዳንኩ ዋኝቼ ወደ ባህር ዳርቻው ልወጣ አልችልም ምክንያቱም በጣም ሩቅ ስለሆነ፡፡

በድንገት ወደ እኔ የሚመጣ ሌላ ጀልባ አየሁ ጀልባው ወደ እኔ እየቀረበ ሲመጣ የመርከቧ ካፒቴን የነፍስ አድን ወደ ውሃው ወረወረልኝ ‹‹ያዘው እኔ ወደ ጀልባ ው እስብሃለሁ›› አለኝ ምን ማድረግ አለብኝ የያዝኩትን እንጨት የተማመንኩበት ን የሙጥኝ ማለት ወይስ እሱን ለቅቄ ነፍስ አድኑን በመያዝ ህይወቴን ማትረፍ? ምን ማድረግ አለብኝ?

እንጨቱ እስከዛሬ ያድነኛል ብዬ ያመንኩትን ነገር ያመለክታል፡፡ ነፍስ አድኑ ጀልባ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ተረጋግተን እየተጠብቀን የምንኖረው አየሱስን በሚወክለው ጀልባ ላይ ነው፡፡ በራሳችን እንገባለን ብለን እንተማመናለን ወይስ በኢየሱስ እኛን ለማዳን በሰራው ስራ የመዳንና እምነት ማለት የዘላለም ህይወት ለማግኘት ኢየሱስን ብቻ እንደግል አዳኝ ማመን ማለት ነው፡፡

ድራማውን ለተማሪዎች በሚመች መልክ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለአንዳንድ ልጆች በወንዝ እና በታንኳ ቢሰራ ሊቀል ይችላል፡፡

ሽምደዳ፡ እምነት የትምህርት ክፍል

ይህን ስጦታ እንዴት እናገኛለን በእምነት

የመዳን እምነት ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ማለት ብቻ አይደለም፡፡
የመዳን እምነት ለአሁን ብቻ አይደለም፡፡
የመዳን እምነት ኢየሱስን የዘላለም ህይወት እንደሚሰጥ
በግል ማመን ማለት ነው፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና
ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ (የሐዋ 16፡31)

(የጀልባው ታሪክ በጀልባ ውስጥ ብቻዬን ነኝ እንበል)
ይህን ነገር ተረደተሃል

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፍ ገጽ 21፣ 22 እና 23 ያለውን ተግባር አከናውን፡፡
- ልጆች ከመሪዎቻቸው ጋር የእምነት ትምህርት ክፍልንና የጀልባውን ታሪክ እንዲለማመዱት አድርግ፡፡
- በጋራ መጸለይ፡፡

የቤት ስራ

የቤት ስራቸውን ቀድመው የጨረሱ ልጆች የወንጌልን ጎዳና መለማመድ መቀጠል ይችላሉ፡፡

- ጀልባዋን በአካባቢያችሁ በሚገኙ ቁሳቁሶች በመስራት ልጆች በጊዜያዊ እምነት እና መዳን እምነት መካከል ያለውን ልዩነት ከሌላ ሰው ጋር እንዲከፋፈሉ አበረታታ.

ፀሎት

ጌታ ኢየሱስ ሆይ የዘላለም ህይወት ስጦታና አንተን በማመን ስለምትሰጠን እናመሰግ ናለን፡፡ አሜን!



ምዕራፍ 11፡ ምላሽ



የትምህርት ግቦች

- ልጆች ሰዎች ለወንጌል ምላሽ እንደ ሚሰጡ ይረዳሉ።
- አንዳንዶቹ ኢየሱስን ለመከተል ቁርጠኞች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ዝግጁ አይሆኑም።
- ቁርጠኝነት ማለት ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝና ጌታን መቀበል ከኃጢአት መራቅ እና ኢየሱስን መቀበል መሆኑን ይረዳሉ።
- ልጆች ቁርጠኝነት ምን ማለት እንደሆነና በራሳቸው ህይወት ውስጥ ያለውን ትርጉም ማካፈል ይችላሉ።
- ልጆች የምላሽ የትምህርት ክፍሉን ከእጅ እንቅስቃሴው ጋር በማለት ይደግሙታል።

እንኳን ደህና መጡ፣ ፀሎት፣ ምስጋናና መዝሙር

የልደቱ አበባበር ሊጀመር ነው።

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ በመከለስ ልጆች እንዴት የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለሌሎች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት መጠየቅ።

የመምህሩ እና የቡድን መሪዎች ዝግጅት

በምዕራፍ ሁለት ላይ በልጆች የተሞላውን የተሰጠውን ጥያቄ መልሶች መምህሩ በተገቢ ሁኔታ ይመለከታል ይከልሳል። የሰጡትን መልስ በገጽ 26 የተግባር መጽሐፍ ላይ ከሰጡት ምላሽ ጋር በማወዳደር ከቡድን መሪዎቹ ጋር በግል ተወያዩበት። መንፈስ ቅዱስ በመራህ መጠን ከቡድን መሪዎቹ እገዛ ጋር ልጆች ስለ ኢየሱስ የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ ወይም የተማሩትን የበለጠ መረዳት ከፈለጉ ልታገኛቸው እንደምትችል አሳውቅ።

ልጆች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን ነገር ግን በምንም አይነት የተጫንካቸው ወይም ያስገደድካቸው መስሎ ሊሰማቸው አይገባም። ለመንፈስ ቅዱስ በህይወትቸው ለሚሠራው ስራ ሁልጊዜም ንቁና ዝግጁ ሁን።

የማስተማሪያ ነጥቦች

ውይይት፡ ምላሽ እና ቁርጠኝነት

- ምላሽ ማለት ምን ማለት ነው?

  ወንጌልን ለሌሎች በምታካፍለበት ጊዜ በቁርጠኝነት ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ምላሽ መስጠታቸው የማይቀር ነው። አንዳንዶቹ አስበውበት ሊመልሱ ይችላሉ። ምንም ችግር የለውም። እኛ በመናገራችን ብቻ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት አሳይተናል የተቀረው በእግዚአብሔር እጅ ነው።

- <u>ቁርጠኝነት</u> ማለት ምን ማለት ነው?

  ቁርጠኝነት ማለት ውሳኔ ወይም በዚያ መቀጠል ማለት ነው፡፡ ለኢየሱስ ቁርጠኛ መሆን ማለት ከምንሰራው መጥፎና ኃጢአተኛ ስራ በመመለስ በኃጢአቱ በማዘን ኢየሱስ እንደሚያድን ማመን ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ከልብ የመነጨና ለዘለአለም የሚቀጥል ሲሆን ለኢየሱስ ቁርጠኞች ስንሆን ኢየሱስን እንደ አዳኝና ጌታ በህይወታችን እናምነዋለን ማለት ነው፡፡

  ይህ ምን ማለት ነው?

- ኢየሱስ እንደ አዳኝ ከኃጢአት ቅጣት አድኖናል፡፡ የኢየሱስ ፍጹም ህይወት እና መስዋዕትነት እኛ የዘላለም ህይወት እንድናገኝ አድርገናል፡፡

- እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደንከተለው ጠርቶናል፡፡ ይህን ለማድረግ ከኃጢአታችን መመለስ አለብን፡፡ ይህ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር ከኃጢአት የምንርቅበትን ፍላጐት በመስጠት እናደርግ የነበረውን ትተን በፋንታው እግዚአብሔርን መከተል እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንጂ የእኛን ሃሳብ አናደርግም ኢየሱስ በልባችን በጌትነት ይኖራል፡፡

የዘላለም ህይወት የምናገኘው በእምነት እና በኢየሱስ በማመን ነው፡፡ በፀሎት ቁርጠኝነት ማሳየት እምነታችንን የምናሳይበት አንዱ መገለጫ ነው፡፡

የመምህሩ ማስታወሻ

አንድ ልጅ ወንጌል ሰምቶ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆነ መጸለያችሁን አታቋርጡ ምክን ያቱም እግዚአብሔርን እና እንዴት እንደሚይምኑ ገና እየተማሩ ስለሆነ ነው፡፡

በገጽ 22 ምዕራፍ 4 ላይ የሚገኘውን የአትክልተኛውን ማብራሪያ አመሳክር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡ መዳን

የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ እና መወያየት የሐዋ 16:31፣ ሮሜ 10:9፣ ዮሐ 6:47

ድራማ፡ የሁለት ወንበሮች ቀልድ

አንድ መሪ ጠንካራ በሆኑ ሁለት ወንበሮች ላይ ይቆማል (አንደኛው ኢየሱስ ሁለተናው ደግሞ እኔ የሚል ምልክት ይደረግበታል)፡፡ መሪው አንድ እግሩን አንደኛው ወንበር ላይ ሁለተኛ እግሩን ሌላኛው ወንበር ላይ ያደርጋል፡፡ ሁለት ሌላ መሪዎች መምህር ሲናገር እኔ የሚለውን ወንበር ለመሳብ ይዘጋጃሉ፡፡

የመሪው ቀኝ እግር ኢየሱስን በወከለው ወንበር ግራ እግሩን ደግሞ ራሱን በሚወክለው ወንበር ላይ ነው ያለው እንበል፡፡ መሪው እኔ የሚለውን ወንበር ቀስ ብሎ በመግፋት ቀስ በቀስ ወደ አንደኛው ወንበር ላይ ይቆማል፡፡ ሙሉ በሙሉ ክብደቱን መሸከም ወደሚችለው ወንበር፡፡ ኢየሱስ የሚለውን ወንበር አምኖ ሁለቱንም እግሮቹን እዚያ ወንበር ላይ ያደርጋል መሪዎቹ እኔ የሚለውን ወንበር ቀስ በቀስ ይስባሉ፡፡

ተመለከታችሁ ሁለቱም ጋር መሆን አንችልም፡፡ በእኛ እና በኢየሱስ ላይ በአንድነት ሆነን ኢየሱስን ብቻውን እናምነዋለን ልንል አንችልም፡፡ ቁርጠኝነት ማለት ተስፋችንን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ እና ለእኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ ባደረገው ነገር ላይ ማድረግ አለብን፡፡ መሪዎች እኔ የሚለውን ወንበር አርቀው በመውሰድ መሪው አንደኛው ወንበር ላይ ብቻ እንዲቆም ያደርጉታል፡፡ መሪው ሙሉ በሙሉ በቁርጠኝነት ኢየሱስ የሚለው ወንበር ላይ ቆሟል፡፡ እምነታችሁን ማን ላይ ነው ያደረጋችሁት ብለህ ተማሪዎቹን ጠይቅ፡፡

ለመጨረስ ሮሜ 10 :9 ማንበብ

መሸምደድ፡ የምላሽ የትምህርት ክፍል

ይህ ምን እንደሆነ ተረድተሃል?
ኢየሱስ ኃጢአትህን ይቅር
እንዲልህና የዘላለም ህይወት
እንዲሰጥህ መጠየቅ ትፈልጋለህ?

ይህ ማለት በኢየሱስ ማመን ከኃጢአት መራቅ

እና ኢየሱስን መከተል ማለት ነው፡፡

ይህን ነው የምትፈልገው? ከሆነ አብረን መፀለይ እንችላለን፡፡

‹‹ጌታ ኢየሱስ ሆይ ኃጢአቴን ይቅር በል
ጌታዬ እና አዳኜ ሆነህ ወደ ህይወቴ ግባ አሜን፡፡››

‹‹በእኔ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው›› (ዮሐ 6፡47)

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መጣህ

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፍ ገጽ 24፣ 25 እና 26 ላይ ያሉትን ተግባራት አከናውን
- ልጆች ምላሽ የሚለውን የትምህርት ክፍል ከመሪዎቻቸው ጋር እንዲለማመዱ አድርግ፡፡
- በጋራ መጸለይ ፡፡

የቤት ሰራ የእጅ ስራ

የቤት ስራቸውን የጨረሱ ልጆች የወንጌል መንገድ ትምህርትቸውን መለማመድ ይችላሉ፡፡

የዘላለም ህይወት ጥቅም (የተግባር የቤት ሰራ መጽሐፍ)
ቁርጠኛ ስንሆን የምናገኛቸው ጥቅማ ጥቅሞች አሉ፡፡ በቁርጠኝነታችን ከምናገኘው ትልቁ ጥቅማ ጥቅም ዋናው ኢየሱስ አዳኝና ጌታ ይሆናል፡፡ እኛንም ለመርዳት ሁል ጊዜ በቅርበት ይሆናል፡፡ የቡድን መሪዎች የቤት ስራዎቹን ከልጆቹ ጋር ይወያዩባቸዋ ል፡፡ በመቀጠልም በእያንዳንዱ ጠረጴዛ ለይ በወረቀት ከዘላለም ህይወት የምናገኘውን ጥቅም ጥቅሱን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማውጣት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ ከመሪዎቻቸው ጋር ከተወያዩ በኋላ እያንዳንዱ ልጅ ለራሱ ትርጉም የሰጠውን የወደደውን ጥቅም ቆርጦ በማውጣት የስጦታ ሳጥኑን ያስጌጥበታል፡፡

ልጆች የዘላለም ህይወትን ጥቅም ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እንዲከፋፈሉ ማበረታታ፡፡

ፀሎት

በሰማይ ያለህ አባታችን የዘላለም ህይወትን ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን ሁልጊዜ እንድናገለግ ልህ እርዳን፡፡ አሜን !

ምዕራፍ 12፡ በኢየሱስ ማደግ



የትምህርቱ ግቦች

- ልጆች እግዚአብሔር የበለጠ እንድናውቀው እንደሚፈልግ እና ለፍቅሩም ምላሽ እንድ ንሰጠው እንደሚፈልግ ልጆች እንዲረዱ፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ በፀሎት በአምልኮ በህብረት እና በሌሎች ወን ጌልን በመናገር በኢየሱስ ያድጋሉ፡፡
- ልጆች ወንጌልን ለመናገር ፍቃደኞች እና አቅም ያላቸው ይሆናሉ፡፡

እንኳን ደህና መጡ፣ ፀሎት፡ ምስጋናና መዝሙር

አበባ ያለው ጤነኛ አትክልት እና እየጠወለገ ያለ አበባ አሳይ፡፡

ክለሳ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በመከለስ ልጆች እንዴት የቤት ስራቸውን የተማሩትን ለሌሎ ች ለማካፈል እንደተጠቀሙበት ጠይቅ፡፡

የማስተማሪያ ነጥቦች

በኢየሱስ ለማደግ የሚያስፈልጉት አምስት መንገዶች የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ፣ መጸለይ፣ ማምለክ፣ ህብረት ማድረግ እና ለሌሎች ስለ ኢየሱስ መናገር ናቸው፡፡

ማብራሪያ፡ አትክልት ማሳደግ

አበባ ያለው ጤነኛ አትክልት በአማራጭነት በመጠቀም አበባ ለማደግ ምን ምን እንደ ሚያስፈልገው (ውሃ፣ የፀሃይ ብርሃን፣ ለም አፈር ወዘተ) ተወያዩ ውሃ የማያገኝ አትክል ት ምን ይሆናል) ‹‹የተጠማ›› አትክልት አይተህ ታውቃለህ) አትክልቱ ምን ይመስላል) የበሰለ አትክልት ምን አለው ፍሬ ወይስ አበባ)

ዮሐ 15፡10 ሲናገር ‹‹ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ፡፡››

ገላትያ 5፡22 መናገር ‹‹የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት ቸርነት በ ጐነት እምነት የዋህት ራስን መግዛት ነው፡፡››

በህይወታችን ፍሬ ማፍራት ካለብን በሳል ክርስቲያኖች መሆን ይኖርብናል፡፡ እግዚአብ ሔር እንድናድግና ፍሬ እንድናፈራ ይፈልጋል፡፡

ማብራሪያ፡ ንቦች ቢራቢሮዎች (በአማራጭነት)

አበባውን በማሳየት አንድ ትንሽ ነገር ይህ አበባ እንዲያብብ እና እንዲራባ እንዳደረግ ታውቃለህ) ይህ ትንሽ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ) ንብ ወይም ቢራቢሮ ነው፡፡ ንቦቹ እና ቢራቢሮዎቹ ከአንዱ አበባ የዘር ብናኝ ይዘው ወደ ሌላው በመሄድ አበቦች እንዲራቡ እና እንዲያብቡ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም አማካኝነት በሚቀጥለው አመት አዳዲስ እና የሚያሳምሩ አበቦች ይፈጠራሉ፡፡ ልክ እንደ ንቦቹ ቢራቢሮዎቹ እግዚአብሔር እና ንቱንም ወንጌልን ለሌሎች እንደታደርሱ ይጠቀምባችኋል፡፡ አበባ ባያችሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ነገር አስታውሱ፡፡

ውይይት፡ የማደግ አምስት መንገዶች

የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ፣ በመጸለይ፣ በማምለክ፣ ህብረት በማድረግ፣ ለሌሎች ስለ ኢየሱስ በመናገርና በእምነት ልናድግ እንችላለን፡፡

- መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ

መጽሐፍ ቅዱስ በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሔርን የበለጠ እናውቀዋለን፣ ማን እንደሆነ እናውቃለን፡፡ እንዴት መኖር እንዳለብን እንደሚፈልግ እናውቃለን፣ ስለ ኢየሱስ እና ስለ ፍቅሩም የበለጠ እናውቃለን፡፡ (2ጢሞ 3፡14-17 ዕብ 4፡12 መዝ 119፡105)

- ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት መንገድ

ከእግዚአብሔር ጋር ልናወራው የማንችለው ነገር አለ) በምንጸልይበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር እናወራለንም እሰማዋለንም፡፡ ወደ ኢየሱስ የቀረበ ህይወት ለመኖር ከፈለግን በታማኝነት ልንፀልይ ይገባል በቀን ውስጥ ወጥ የሆነ የጸሎት ሰዓት ቢኖረን ጥሩ ነው በተጨማሪ በፈለግነው ሰዓት መፀለይ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንችላለን፡፡ (ማቴ 6፡5-15፡ 1ተሰ 5፡17 ኤፌ 6፡10-18)

- አምልኮ እግዚአብሔር ማድነቅ ማመስገን ማክበር ፍቅርን መግለጽ፡፡ ቤተክርስቲያንን ጨምሮ እግዚአብሔርን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የበለጠ ለማወቅ እንበረታታለን፡፡ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ለማመስገንና በእውነት እና በመንፈስ ለማድነቅ የሚሰበሰቡበት ጉባኤ ነው፡፡ እኛም በቤተክርስቲያን ተግባራት በመሳተፍ ለእግዚአብሔር መንግስት ስራ የበኩላችንን ማድረግ እንችላለን ፡፡ (መዝ 66፡4፡ መዝ 95፡6፡ ዕብ 10፡24-25 ዮሐ 4፡24)

- ህብረት: ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ጓደኝነት መፍጠር፡፡ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በምንሆንበት ጊዜ አብረን መጸለይ፡ እርስ በእርሳችን መዋደድ ለክርስቶስ መኖር አንዳችን አንዳችንን ማበረታት እንችላለን፡፡ (ዕብ 10፡24-25፣ 1ዮሐ 1፡7፣ ዮሐ 13፡34-35፣ ገላትያ 5፡13)

- ምስክርነት ስለ ኢየሱስ ለሌሎች መንገር፣ ለሌሎች ስለ ኢየሱስ በምንናገርበት ጊዜ እንዴት የዘላለም ህይወት እንደሚያገኙ እናሳያቸዋለን፡፡ እግዚአብሔር በህይወታቸው ሲሰራ ደግሞ የእኛ እምነት እና ፍቅር በእግዚአብሔር ላይ ይጠነክራል፡፡

ጨዋታ (በአማራጭነት)፡ አካባቢው ላይ በተለመደ ጨዋታ አምስቱን የዕድገት መንገዶች ማስተማር

መሸምደድ፡ በኢየሱስ ማደግ

የተጠቀሙት የእጅ ምልክት ተግባራት ልጆች አምስቱን የክርስቲያን እድገት መንገዶ ች እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ
(የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ መያዝ እጅ መዘርጋት)

ፀሎት
(እንደሚጸለይ እጅን ማድረግ)

አምልኮ
እንደሚዘመር አይነት እጅን ወደላይ ከፍ ማድረግ

ህብረት
(በቀኝ እጅ የሌላውን እጅ መጨበጥ)

ምስክር
(በእጅ የመናገር ምልክት ማሳየት)

ይህን ሁሉ የምናደርገው ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር እና ሌሎችንም ስለምንወድ መሆኑን አስታውስ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ እሱ ቀድሞ ስለወደደን ነው፡፡

ማበረታትት፡ የምስራቹን ቃል ለማካፈል

ኢየሱስ ወንጌልን ለሌሎች እንድናካፍል ይፈልጋል ኢየሱስ በልባችሁ ካለ ወንጌልን ስለ እርሱ ለሌሎች መናገር ትፈልጋላችሁ፡፡ በክፍል ውስጥ የተዘጋጁትን የቤት ስራ ዎች በማሳየት የቤት ስራዎቻችንን እንዴት ወንጌልን ለመናገር እንደምንጠቀምባቸው ተምረናል፡፡

- የምስራቹን ቃል ተምረናል (ምዕራፍ 4)
- ለሌሎች የምናካፍለው ምስክርነት አለን (ምዕራፍ 5)
- ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆንን እና አዳኝ እንደሚያስፈልገን ለሌሎች መናገር (ምዕራፍ 7)
- እግዚአብሔር አፍቃሪ እና ትክክለኛ መሆኑን ለሌሎች መናገር (ምዕራፍ 8)
  እግዚአብሔር አፍቃሪ እና ትክክለኛ መሆኑን ለሌሎች ማካፈል (ምዕራፍ 11)

የወንጌል መጽሐፍ

በተስፋ ለህፃናት ወርክሾኘ ላይ ይህን መጽሐፍ እንዴት መጠቀም እንደምትችል ተምረሃል ሰልጥነሀል ወንጌልን ለቤተሰቦቻቸው እና ለጓደኞቻቸው መናገር እንዲችሉ መጽሐፉ ለእያንዳንዱ ልጅ ይሰጣል፡፡

የቡድን ሰዓት

- በተግባር መጽሐፉ ገጽ 27 እና 28 ያሉትን ተግባራትን አከናውን፡፡
- በጋራ መጸለይ

የቤት ስራ



- **የወንጌል የጨሌ አምባር**
  ልጆች በኋላ ወንጌልን ለማካፈል የሚረዳቸውን የወንጌል የጨሌ አምባር ይሰራሉ፡፡ በማብራሪያው በወንጌል የተስፋ ለህፃናት ላይ በተመለከተው መሠረት የተለያየ ቀለም ያላቸው ጨሌዎችን በክር በማስገባት መስራት ይቻላል፡፡

  - መንግስተ ሰማይ = ወርቅ (የ ወርቅ ጐዳና) ራዕይ 21፡ 18-21
  - ኃጢአት=ጨለማ (ሁላችንም ኃጢአተኞች) ነን 1ዮሐ 1፡5
  - እግዚአብሔር ንፁህ እግዚአብሔር ፃድቅ ነው ዮሐ 1፡5
  - ክርስቶስ=ቀይ (የክርስቶስ ደም) ዮሐ 19፡34
  - እምነት=ሰማያዊ (የጀልባው ታሪክ) ማቴ 14፡27-29
  - ምላሽ =አረንጓዴ (እድገት) ራዕይ 22፡2

  ማስታወሻ፡ የቀለሙን ምርጫ በባህሉ በአካባቢው ልማድ እና በአካባቢው በሚ ገኘው ዕቃ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

  ### ዘር (በአማራጭነት)

  ልጆች እንዲተክሏቸው ዘሮች መስጠት (ማር 4፡1-8)

ልጆች የወንጌል የጨሌ አምባራቸው እና ሌላ የሰሯቸውን የቤት ስራዎችን በመ ጠቀም ወንጌልን ለሌሎች ሰዎች እንዲናገሩ አበረታታቸው፡፡ በተጨማሪም ለሌ ሎች መንገር የሚሰጠውን ደስታና እኛንም በእምነታችን እንደሚያሳድገን አስታ ውሳቸው፡፡

እንደማጠቃለያ ልጆች ለወላጆቻቸውና ለጓደኞቻቸው ወንጌል በሚናገሩበት የመጨረሻ እና አዝናኝ ዝግጅት ላይ ወላጆች ጓደኞችና ቤተሰቦቻቸውን በመጋበዝ ተሳታፊ ማድረግ፡፡

ፀሎት

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ልጆችህ እንድንሆን ስለ መረጥከን እናመሰግንሃለን፡፡ ስለ አንተ የበለ ጠ እንድናውቅ እና የበለጠ እንድንወድህ እንዲሁም ስለ ዘላለም ህይወት ለሌሎች እንድንናገር እርዳን፡፡ አሜን!

ትግበራ

የተስፋ ለህፃናት የመተግበሪያ መመሪያ

ይህ የምስራቹን ቃል ለማካፈል የሚያስችል አስደናቂ መንገድ መጀመሪያ ነው። ይህ የስራ መመሪያ የተስፋ ለህፃናት ጋር የምትሰራውን ራዕይ እንዲሰጥህ ፀልይ

1. ፀሎት

- የስራ መመሪያ የተስፋ ለህፃናት ጋር የምትሰራውን ራዕይ እንዲሰጥህ ፀልይ።
- ራዕይህን ከመሪዎች እና ቤተክርስቲያንህ ከተስፋ ለህፃናት ጋር የምትሰራውን ራዕይ ተወያይበት።
- አብረውህ የሚፀልዩ ሁለት የጸሎት ጓደኞች አዘጋጅ።

2. የጊዜ እቅድ ማውጣት

የተስፋ ለህፃናት ፕሮግራም በቀላሉ ሊራመድ የሚችል በመሆኑ ፕሮግራሙ ከቤተክርስቲያን ቤተእምነት ጋር እንዲጣጣም የቀንና የጊዜ እቅድ አውጣ።

☐ 12 ሳምንት ☐ 6 ወራት
☐ 12 ወራት ☐ የእሁድ ትምህርት
☐ የበዓላት መጽሐፍ ቅዱስ ☐ ሌሎች _____

የመጀመሪያ ቀን: _____ የማጠናቀቂያ ቀን : _____

በየሳምንቱ የትምህርት ጊዜ : _____ _____

3. ቦታውን ማሰናዳት

የተስፋ ለህፃናት ትምህርት የት እንደምታስተምር ወስን።

ቦታ፡ _____ _____

4. የቡድን መሪዎችን ማዘጋጀት

ለቡድን መሪዎች መመልመያ መስፈርቶች (ረዳቶች)

- እምነት የሚጣልበት በቀላሉ የሚገኝ እና ለማስተማር ቀላል
- የተስፋ ለህፃናት የወንጌል ጐዳናን ለማስተማር እና አርአያ ለመሆን ፍቃደኝነት
- ለልጆች ለመፀለይ ፍቃደኛ መሆን
- በስራ ላይ ልምምድ ወቅት ወንጌልን ለማካፈል ፈቃደኝነት
- እምነት የሚጣልበት
- ለልጆች
- አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ የጀርባ ጥናት ቢካሄድ ፈቃደኛ መሆን

የቡድን መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ልጆችን ስም መያዝ

_____

_____

5. **ለህዝብ ማስተዋወቅ**

ለጉባኤ እና ለልጆች ወላጆች የተስፋ ለህፃናት ፕሮግራም በደንብ መተዋወቅ አለበት፡፡

- የተስፋ ለህፃናት ስልጠና እንዴት ነው ለጉባኤ ሊነገር የሚችለው?

_____

- የተስፋ ለህፃናት ስልጠና መቼ ነው ለጉባኤ የሚነገረው?

_____

- ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ጨዋታዎች›› እንዴትና መቼ ነው የሚታተሙት?

_____

6. **ቁሳቁሶችን ማሰናዳት**

- እያንዳንዱ ምዕራፍ ለቤት ስራዎቹ ቁሳቁሶች ስለሚያስፈልጉት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቁሳቁሶች አሟላ፡፡
- አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ከአካባቢ መፈለግ ወይም ማዘጋጀት ሌሎችም በስራ ው እንዲያግዙ ማድረግ፡፡
- ለአውደ ጥናት የሚያስፈልጉ ነገሮች ዝርዝር:
  - የተግባር መጽሐፍና የተስፋ መንገድ ለእያንዳንዱ ልጅ መድረሱ
  - የወንጌል መንገድ፣ የምስራች ቃል እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መለጠፊ
  - አካባቢውን ማስጌጥ
  - እስራስ፣ መቀስ፣ ማጣበቂያና ከለሮች
  - አሻንጉሊቶችን በእያንዳንዱ ትምህርት ላይ የሚያስፈልጉ
  - የእጅ ስራ ምሳሌዎች

7. **የስራ ላይ ልምምድ ዕቅድ ማውጣት**

- የስ.ላ.ለ የት እና መቼ ነው የምታካሂደው?
- ሁልጊዜም አስተማማኝ፣ የተስተካከለ እና ሙሉ ቁጥር ያለው መሆኑን የምታካሂደው

8. **የወንጌል መጽሐፍትን እና የአምላክ/ ሰው ፊልምን በመጠቀም የወ ሰነ ትምህርቱን መጨረሻ እቅድ አውጣ፡፡**

የራስህን የተስፋ ለህፃናት የወሰነ ትምህርት ሰንጠረዥ አዘጋጅ!

የትምህርቱን ዕቅድ ስንጨርስ ዝርዝሩን በምሳሌው ላይ እንዳለው በሰንጠረዥ ላይ አስፍር፡፡ ሰንጠረዥ የትምህርት ዕቅዱን ለማውጣት አጋዥ ሊሆን ይችላል፡፡

ምዕራፎች	እንኳን ደህ ና መጡ	ታሪክ	ድራማ/ ማብራሪያ	የተግባር መጽሐፍ ተግባር /የእጅ ስራ/ የቤት ስራ	መዝሙሮች
1 .የመጽሐፍ ቅዱስ ጨዋ ታዎች					
2 ቃለ ምልልስ					
3 የወንጌል መንገድ					
4 የምስራች ቃል					
5 እንነጋገር					
6 መንግስተ ሰማያት					
7 ኃጢአት					
8 እግዚአብሔር					
9 ክርስቶስ					
10 እምነት					
11 ምላሽ					

ተጨማሪ ማብራሪያዎች

የተስፋ ለህፃናት የወንጌል መንገድ

በጣም መልካም ዜና አለኝ

መንግስተ ሰማያት

መንግስተ ሰማይ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ በስራውም ስለተገባን የምናገኘው አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው በእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ የዘላለም ህይወት ነው ...ሮሜ 6፡23

ፀጋው በእምነት አድኖአችኋል ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም፡፡ ኤፌ 2፡8-9

(የጎደኛ ስጦታ ታሪክ)

ይህንን ስጦታ እንዳናገኝ ያገደን ነገር ምንድን ነው?

ኃጢአት

ሁላችንም ራሳችንን ማዳን አንችልም ምክንያቱም ሁላችንም ኃጢአት ሰርተናል፡፡

ሁሉም ኃጢአት ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐሏቸዋል ሮሜ 3፡23

(የተበላሸው ታሪክ)

የተለየ መንገድ መኖር አለበት - የእግዚአብሔር መንገድ!

እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ቅዱስ፣ የፍቅር አምላክና ትክክል (ፍትኃዊ) ነው፡፡ በአንድ በኩል እግዚአብሔር ስለሚወደን ሊቀጣን አይፈልግም፡፡ በሌላ በኩል ግን እግዚአብሔር ትክክል/ ፍትሃዊ ስለሆነ ኃጢአትን መቅጣት አለበት፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው 1ዮሐ 4፡

(በአማራጭ) *ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ አይተውም ዘፀ 34፡7*

የቅጣቱ ታሪክ

ችግሩ ይታያችኋል?

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን በመላክ ይህን ችግር ፈታው፡፡

ክርስቶስ

ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡ ከሰማይ ወደ ምድር በመምጣት በምድር ላይ ፍፁም ህይወት ኖሮ ስለ እኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ ሞተ፡፡ ነገር ግን ከሙታን ተነሳ አሁን በሰማይ ሆኖ የዘለአለም ህይወት ግብጣ ያቀርብልሀል፡፡

እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዷልና፡፡ ዮሐ 3፡16

(የኃጢአት መጽሐፍ ታሪክ)

ይህን ስጦታ እንዴት እናገኛለን? በእምነት

እምነት

የመዳን እምነት ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ ማለት አይደለም፡፡

የመዳን እምነት ለአሁን ብቻ አይደለም ፡፡
የመዳን እምነት ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ህይወት እንደሚሰጥ ብቻውን ማመን ነው፡፡
በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተ እና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ የሐዋ.16፡31
(የጀልባው ታሪክ)
ይህ ነገር እየገባህ ነው?

ምላሽ

ኢየሱስ ኃጢአትህን ይቅር እንዲልህና የዘላለም ህይወት እንዲሰጥህ ልትጠይቀው ትፈ ልጋለህ) ይህ ማለት በኢየሱስ እመን ከኃጢአት ተመለስ ዳግመኛም አታድርገው ማለት ነው፡፡ ይህንን ነው የምትፈልገው) ከሆነ አብረን መፀለይ እንችላለን፡፡
ውዱ ኢየሱስ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡፡ የህይወቴ አዳኝና ጌታ ሁን አሜን!
በእኔ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው፡፡ ዮሐ 6፡47

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በሰላም መጣህ!

የተሙዋላ ተስፋ ለልጆች የወንጌል ፈለግ ሲገለፅ

መነጋገር እና ምስክርነት

ንገረኝ፡ ስለ እግዚአብሔር አስበህ ታውቃለህ?
እግዚአብሔር አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት አብረነው እንድንሆን ይፈልጋል፡፡

ያንተን ታሪክ ተናግር

ሁለት ጥያቄዎች

አንድ ነገር ልጠይቅህ እችላለሁ? አንድ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር በመንግስተ ሰማያት እንደምትሆን በእርግጠኝነት ታውቃለህ?
እግዚአብሔር ለምን ወደ መንግስተ ሰማያት አስገባሃለሁ?ቢልህ ምን ትላለህ?

መሸጋገሪያ

በጣም መልካም ዜና አለኝ!

መንግስተ ሰማያት

መንግስተ ሰማይ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ ሰርተህ/ለፍተህ ወይም ስለሚገባህ የምታገኘው አይ ደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ የዘላለም ህይወት ነው›› ሮሜ 6፡23
ፀጋው በእምነት አድኗችኋል ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከአንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም፡፡ ኤፌ 2፡8 የጓደኛ ስጦታ ታሪክ
በጣም የቅርብ ጓደኛዬ ስጦታ ቢሰጠኝ እኔ ግን ስጦታውን ዋጋ ለመክፈል ብሞክር
ወይም በስራ ለማካካስ ብሞክር፣ ስጦታ መሆኑ ይቀራል፡፡ በተመሳሳይ መንግስተ ሰማያ ት ለመግባት መክፈል ወይም መስራት የማንችለው፡፡

ይህንን ስጦታ እንዳናገኝ ያደረገን ምንድን ነው?

ኃጢአት

ሁላችንም ኃጢአተኞች ስለሆንን ራሳችንን ማዳን አንችልም

ኃጢአት ምንድን ነው) ኃጢአት ማለት እግዚአብሔርን የማያስደስት፣ የምናስበው፣ የምንናገረው፣ የምንሰራው ወይማ የማንሰራው ነገር ሁሉ ነው።።

‹‹ሁሉም ኃጢአት ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል።።›› ሮሜ 3፡23

የተበላሸ ምግብ ታሪክ፡ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት በመልካም ስራ መሞከር ማለት በተበላሸ ምግብ (ግብአት) ምግብ ለመስራት መሞከር ማለት ነው።። አንድ የተበላሸ ነገር ምንም ሌላው ሁሉ ጥሩ ቢሆን ምግቡን ያበላሸዋል።። በእግዚአብሔር የፍጹምነት መስፈርት አንዲት ኃጢአት ሁሉን ነገር ታበላሻለች።። እንዴት ራሳችንን ማዳን እንደማንችል ተመለከትክ?

የተለየ መንገድ መኖር አለበት።። የእግዚአብሔር መንገድ!

የእግዚአብሔር

እግዚአብሔር ቅዱስ፣ የፍቅር አምላክ እና ትክክል (ፍትሃዊ) ነው።። በአንድ በኩል እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ (ስለሚወድ) ሊቀጣን አይፈልግም።። ግን በሌላ በኩል እግዚአብሔር ትክክል / ፍትሃዊ ስለሆነ ኃጢአትን መቅጣት አለበት።።

‹‹እግዚአብሔር ፍቅር ነው።።›› 1ዮሐ 4፡8 (በአማራጭነት) ‹‹ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ አይተውም።።›› ዘፀ 34፡7

የቅጣቱ ታሪክ፡ የቡድን መሪው የእናቱን ቅጣት እንደተቀጣ ኢየሱስም የእኛን የኃጢአት ቅጣት ተቀጣልን።። እኛ ልክ እንደ መሪው እናት ነን።። ቅጣት ይገባን ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ስለሚወደን እንድንቀጣ አልፈለገም።።

ችግሩ ይታይሃል) እግዚአብሔር ግን ችግሩን ልጁን ኢየሱስን በመላክ ፈታው።።

ክርስቶስ

ኢየሱስ አምላክ ነው።። ከሰማይ ወደ ምድር በመምጣት ፍፁም ህይወት ኖሮ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ሞተ።። ነገር ግን ከሞት ተነስቶ አሁን በሰማይ ሆኖ የዘላለም ህይወት ግብጣ ያቀርባል።። ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለአለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዷልና።።›› ዮሐ 3፡16

የኃጢአት መጽሐፍ ታሪክ፡ ይህ መጽሐፍ ኃጢአቴን ሁሉ ይዟል ብለን እናንስብ።። እግዚአብሔር ይወደኛል ነገር ግን ኃጢአት ስለሚጠላ ከእግዚአብሔር ኃጢአት ለይቶኛል።። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ወደ ዓለም ላከው።። እግዚአብሔር የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ ኢሳ 53፡6 ኃጢአቴ ሁሉ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአቴ በሞተው በኢየሱስ ላይ ሆነ።። አሁን የኃጢአቴ ዋጋ በመከፈሉ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ እችላለሁ።። እግዚአብሔር አሁን ለእኔና ለአንተ የዘላለም ህይወትን ይጋብዛል።።

ይህን ስጦታ እንዴት እናግኘለን-እምነት

እምነት

የመዳን እምነት ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ አይደለም።።

የመዳን እምነት የአሁን ብቻ አይደለም።።

የመዳን እምነት ማለት ኢየሱስ ብቻውን የዘላለም ህይወት እንደሚሰጥ ማመን ማለት ነው።።

‹‹በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ›› ሐዋ 16፡31

የጀልባው ታሪክ፡ ከመሬት እርቄ ጀልባዬ (የራሴን መልካም ስራዎች ይወክላል) ላይ በባህር ላይ ስንንዝ ጀልባዬ ተሰበረ እና መስጠም ጀመረ መወንጀት ስለማልችል መስጠም ጀመርኩ።። በድንገት የነፍስ አድን ጀልባ (ኢየሱስን ይወክላል) ወደ እኔ መጣ።። የራሴን መልካም ስራ መተው እንዲያድነኝ በክርስቶስ ብቻ ማመን አለብኝ።።

ይህ ነገር እየገባህ ነው?

ምላሽ

ኢየሱስ ኃጢአትህን ይቅር እንዲልህ እና የዘላለም ህይወት እንዲሰጥህ ልትጠይቀው ትፈልጋለህ?

ይህ ማለት በኢየሱስ እመን፣ ከኃጢአትህ ራቅ ኢየሱስንም ተከተለው።።

ይህንን ነው የምትፈልገው) ከሆነ አብረን መጸለይ እንችላለን።።

ውዴ ኢየሱስ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል።። የህይወቴ አዳኝና ጌታ ሁንልኝ አሜን!

ኢየሱስ ሲናገር ‹‹በእኔ የሚያምን የዘላለመ ህይወት አለው›› ዮሐ 6፡47

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በሰላም መጣህ!

በኢየሱስ ማደግ

በእግዚአብሔር ቃል፣ በፀሎት፣ በአምልኮ፣ ህብረት በማድረግ እና በመመስከር በኢየሱስ ልናድግ እንችላለን?

ዓለማቀፍ የወንጌል ትንታግ

ኢንተርናሽናል የእምነት መግለጫና መርሆዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት እንከን የሌለው ኃይለኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው።።
2. ለዘላለም የሚኖር በሶስት ስብዕና ያለው አንድ አምላክ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው፡
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም ነው።። ከድንግል ተወልዶ፣ ኃጢአት የሌለበት ህይወት ኖሮ፣ ተዓምራቶችን አድርጎ፣ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ደሙን አፍሰሰ።። በስጋ ከሞት ተነሳ አሁን በአብ ቀኝ ተቀምጧል።። በክብርና በስልጣንም ተመልሶ ይመጣል።።
4. በመንፈስ ቅዱስ እንደገና መወለድ ለመዳን እና ከኃጢአት ለመንፃት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።።
5. የዘላለም ህይወት የሚገኘው በእምነት ነው።። ይህም ማለት ኢየሱስ ብቻውንእንደሚያድን ማመን ማለት ነው።።
6. መንፈስ ቅዱስ ባመኑ ሰዎች ውስጥ በማደር እግዚአብሔር የሚፈልገውን ህይወት እንዲኖሩ ይረዳቸዋል።።
7. የሚጠፉትም ሆነ የሚድኑት ሁለቱም ከሞት ይነሳሉ እነዚህ ለዘላለም ህይወት አግኝተው ሲነሱ እነዚያ ለዘላለም ጥፋት ይነሳሉ።።
8. በክርስቶስ እውነተኛ አማኞች ውስጥ መንፈሳዊ ህብረት ይኖራል።።
9. አጥቢያ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር የተመሰረተችበት ዋነኛ ምክኒያት ወንጌልን ለዓለም እንድታደርስ ነው።።
10. ማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን በክርስቶስ የተሰጠው ዋነኛ ተልዕኮ በሰዎች ሁሉ ወንጌልን እንድንሰብክና ደቀመዝሙር እንዲያደርግ ነው።።
11. ከህይወት ተሞክሮ የወጡ ምስክርነቶች ወንጌልን ለመናገር በደቀመዝሙርነት ቡድን ውስጥ ጥሩ መንገዶች ሲሆኑ የመስክ ልምምድ ላይ ተገኝቶ ምስክርነት መስጠት የተሻለ ልምምድ ያጎናጽፋል